# ፀሐይ ፡ መስፍን

ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ።



በቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ፀሐይ ፡ መስፍን

## ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ።

በቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው።

፲፱፻፳ ዓ. ም.

ለሁለተኛ ጊዜ በቅዱስ ጊዮርጊስ ማተሚያ ቤት ታተመ ።



የካቲት ፡ ፲፪ ፡ ኣደባባይ ።

ገንዘባችሁ ፡ ባልሆነው ፡ ገንዘብ ፡ ወዳጅ ፡ ግዙበት ፡ ያለውን ፡ የመድኃኒታችንን ፡ ቃል ፡ ልጆቹ ፡ ፈጽመው ፡ ስላገኛቸው ፡ መርቆ ፡ የሰላም ፡ እንቅልፍ ፡ አንቀላፉ ።

# ማውጫ

ምዕራፍ ፡ ፩ ፡............................................................5
ምዕራፍ ፡ ፪............................................................10
ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ............................................................18
ምዕራፍ ፡ ፬ ፡............................................................25
ምዕራፍ ፡ ፭ ፡ ............................................................33
ምዕራፍ ፡ ፮............................................................ 39
ምዕራፍ ፡ ፯ ፡ ............................................................ 44
ምዕራፍ ፡ ፲ ፡............................................................51
ምዕራፍ ፡ ፱ ፡ ............................................................ 58
ምዕራፍ ፡ ፲............................................................ 61
ምዕራፍ ፡ ፲፩ ፡............................................................66
መዕራፍ ፡ ፲፪ ።............................................................72
ምዕራፍ ፡ ፲፫ ፡............................................................ 75

# ምዕራፍ ፡ ፩ ፡

በ፲፱፻፴፩ ፡ ዓመት ፡ ምሕረት ፡ ፀሐይ ፡ ምስፍን ፡ የምትባል ፡ ወጣት ፡ ነበረች ፡ ዕድሜዋም ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ ይሆናታል ።

መልኳ ፡ ቀይ ፡ እጅግ ፡ የምታምር ፡ ቁመትዋ ፡ ዘለግ ፡ ያለ ፡ የተዋበች ፡ ቆንጆ ፡ ከመሆንዋም ፡ በላይ ፡ ደም ፡ ግባትዋና ፡ ቅርጽዋ ፡ ልብ ፡ የሚመታ ፡ መወደድ ይታይባታል ።

ነገር ፡ ግን ፡ ዘወትር ፡ ያዘነችና ፡ አጥቁራ ፡ የምታይ ፡ ወጣት ፡ ነበረች ።

ምክንያቱም ፡ አያትና ፡ ቅድማያትዋ ፡ ከሁለት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በፊት ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ መሳፍንቶችና ፡ አቅኝዎች ፡ ስለነበሩ ፡ ያሁኑን ፡ የስዋን ፡ ኑሮና ፡ የቀድሞ ፡ የቅድማያቶችዋንና ፡ ያያቶችዋን ፡ ትልቅነት ፡ በማመዛዘን ፡ ነው ።

አባትዋም ፡ እንደ ፡ አያቶቹ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ማዕረግና ፡ ካብት ፡ ባይኖረውም ፡ ለቤተሰቦቹና ፡ ለራሱም ፡ የሚበቃ ፡ ትዳር ፡ ነበረው ።

ነገር ፡ ግን ፡ በ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ.ም ፡ ስለ ፡ ሀገሩና ስለ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥቱ ፡ ክብር ፡ በር ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ የክብር ፡ ሞት ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ ጠላት ፡ ካብቱንና ርስቱን ፡ ወርሶ ፡ ትልልቅ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ስለሠራበት ፡ ግርማዊነታቸው ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ ልጁ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ የቤቱን ፡ ግምት ፡ ከፍላ ፡ ለመውሰድ ፡ ካቅምዋ ፡ በላይ ፡ ስለሆነባት ፡ የቦታዋን ፡ ግምት ፡ ብቻ ፡ ወስዳ ፡ ያባትዋን ፡ ቦታ ፡ ለመንግሥት ፡ ለቀቀች ።

የቦታውም ፡ ግምት ፡ አምሳ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ያህል ፡ ይሆን ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ ከጦሩ ፡ በፊት ፡ አባትዋ ፡ አሥራ አምስት ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ከባንክ ፡ ተበድሮ ፡ ስለነበረ ፡ ወለዱና ፡ የወለድ ፡ ወለዱ ፡ ስልሳ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ስለሆነ ፡ በዳኛ ፡ ተከሳ ፡ ኣሥሩን ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ለጉዳይዋ ፡ ስላዋለችው ፡ ዓርባ ፡ ሺውን ፡ ብር ፡ ላባትዋ ዕዳ ፡ ከፍላ ፡

የተረፈውን ፡ ዕዳ ፡ በከተማ ፡ አቅራቢያ ፡ ያለው ፡ ርስቱ ፡ በሐራጅ ፡ ተሸጦ ፡ ለዕዳው ፡ ተከፈለ ፡

ስለዚህ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ሁለት ፡ ጋሻ ፡ መሬት ፡ ብቻ ፡ ተረፋት ።

ይህች ፡ ዕድለ ፡ ቢስ ፡ ወጣት ፡ ሥርታ ፡ እንዳትበላ ፡ አባትዋ ፡ ያስተማራት ፡ የፈረንሣዊ ፡ ቋንቋ ፡ ስለነበረ ፡ ጊዜው ፡ ተለዋውጦ ፡ የእንግሊዝ ፡ ቋንቋ ፡ ስለተስፋፋ ፡ የፈረንሣዊ ፡ ቋንቋ ፡ ለሥራ ፡ መሥራት ፡ የማይረዳት ፡ በመሆኑ ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ ሆና ፡ ተቀመጠች ።

ከእለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ደጉ ፡ ካሣዬ ፡ የሚባል ፡ ፀሐይ ፡ መስፍንን ፡ በመንገድ ፡ ስትናፈስ ፡ ኣይትዋት ፡ በጣም ፡ ወደዳት ፡ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ ከቤትዋ ፡ እየተመላለሰ ፡ ለማግባት ፡ ጠየቃት ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ቀን ፡ የጣላት ፡ የሙት ፡ ልጅ ፡ በመሆንዋ ፡ በጣም ፡ ስለተቸገረች ፡ ይልቁንም ፡ የሚረዳት ፡ ዘመድ ፡ ስላጣች ፡ አንድ ፡ ከመሆን ፡ ሁለት ፡ መሆን ፡ ይሻላል ፡ በማለት ፡ በመንደር ፡ ዳኛ ፡ ካብትሽ ፡ በካቤት ፡ ተባብለው ፡ ተፈጣጥመው ፡ ትጋቡ

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ክብርዋን ፡ ጠብቃ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በንጽሕና ፡ ስለቆየች ፡ ወዲያው ፡ አርግዛ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ወለደች ። ደግሞ ፡ ባመቱ ፡ እንደዚሁ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ወለደች ።

ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ ዓመት ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ ያህል ፡ ከቆየች ፡ በኋላ ፡ አንድ ወንድ ልጅ ፡ ወለደች ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደጉ ፡ ካሣዬ ፡ ጐንደር ፡ ለሥራ ፡ ጉዳይ ፡ ሔዶ ፡ በካሚዮን ፡ አደጋ ፡ ምክንያት ፡ ስለሞተ ፡ ከዚያው ፡ ካንዲት ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ ከምትገኝ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ መቃብር ፡ ቦታ ፡ ተቀብሮ ፡ ለፀሐይ ፡ መስፍን ፡ መርዶው ፡ መጣላት ።


ያቺ ፡ ችግረኛ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ የባልዋን ፡ ሞት ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ መጠን ፡ የሌለው ፡ ኃዘን ፡ አዘነች ። ባል ፡ ሳታገባ ፡ ችግርዋ ፡ የራስዋ

፡ ብቻ ፡ የነበረውን ፡ ሦስት ፡ ሕጻናቶች ፡ ይዛ ፡ ለመኖር ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ሸክም ፡ ወደቀባት ።

በባልዋ ፡ ኃዘንና ፡ በደረሰባት ፡ ችግር ፡ ምክንያት ፡ በማትታወቅበት ፡ አገር ፡ ሔዳ ፡ በገዳም ፡ ለመነኰሳት ፡ ረድ ፡ ሆና ፡ ለመኖር ፡ ብታስብም ፡ እነዚህን ፡ ሦስት ፡ ሕጻናቶች ፡ ጥላ ፡ ለመሔድ ፡ አስጨነቃት ፡

ይልቁንም ፡ አራት ፡ እራስዋን ፡ ሆና ፡ በውድ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ለቤት ፡ ኪራይ ፡ ከፍላ ፡ ለመኖር ፡ የማይዘለቅ ፡ ነገር ፡ ሆነባት ።

ስለዚህ ፡ አቃቂ ፡ በዕቃ ፡ ላይ ፡ ከከተማው ፡ ውጪ ፡ አንዲት ፡ ፎቅ ፡ ቤት ፡ ሁለት ፡ ክፍል ፡ በወር ፡ አራት ፡ ብር ፡ ተከራይታ ፡ ልጆችዋን ፡ ይዛ ፡ ተቀመጠች



ዱከም ፡ የፀሐይ ፡ መስፍን ፡ እርስት ።

ለፀሐይ ፡ መስፍን ፡ አቃቂ ፡ መሔድ ጥቂት የጠቀማት ፡ መሬትዋ ፡ ዱከም ፡ አጠገብ ፡ ስለሆነ ፡ እንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ለማየትና ፡ የሚደርሳትን ፡ እህል ፡ ለመቆጣጠር ፡ ትችል ፡ ነበር ።

ቢሆንም ፡ አሽከር ፡ ስለሌላታ ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ያሉ ፡ ጭሰኞች ፡ በፈቃዳቸው ፡ ብዙውን ፡ ወስደው ፡ ጥቂት ፡ ስለሚሰጥዋት ፡ በመሬትዋ ፡ አልተጠቀመችበትም ፡ ነበር ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ጥቂቶች ፡ ዶሮች ፡ ስላረባች ፡ እንቁላል ፡ ሽጣ ፡ በዚያ ፡ ዋጋ ፡ ወተት ፡ ገዝታ ፡ እነዚያን ፡ የሙት ፡ ልጆች ፡ ትመግብ ፡ ነበር ።

የመኖሪያ ፡ ቤትዋ ፡ ክፍል ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተው ፡ ነው ። የላይኛው ፡ ፎቅ ፡ የፀይ ፡ መስፍንና ፡ የልጆችዋ ፡ መኝታ ፡ ነው ።

ከወደ ፡ ምሥራቅ ፡ በኩል ፡ አንድ ፡ መስኮት ፡ አለው ።

የምድር ፡ ቤቱ ፡ እንግዳ ፡ መቀበያና ፡ የሙብል ፡ ቤት ፡ ነው ።

ከውጪ ፡ አንድ ፡ ዛኒጋባ ፡ ለማብሰያና ፡ ለዶሮ ፡ ቤት ፡ የተሠራ ፡ ያልተለሰነ ፡ ጓዳ ፡ አለ ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ለሚያስፈልጋት ፡ ጉዳይ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በኦቶቡስ ፡ በወጣች ፡ ጊዜ ፡ ልጆችዋን ፡ የሚጠብቅላት ፡ አሽከር ፡ ስለሌላት ፡ ለጐረቤቶችዋ ፡ ልጆችዋን ፡ አደራ ፡ ብላ ፡ ሰጥታ ፡ ቤትዋን ፡ ቆልፋ ፡ ትሔድ ፡ ነበር ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ዘወትር ፡ ወደከተማ ፡ ስትሔድ ፡ በብብትዋ ፡ ሚዜራብልንና ፡ የድሆች ፡ ከተማ ፡ የሚባሉትን ፡ መጻሕፎቶች ፡ ይዛ ፡ በኦቶቡስ ፡ ውስጥ ፡ እያነበበች ፡ ትሔድ ፡ ነበር ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ከኢጣልያን ፡ ወረራ ፡ በፊት ፡ አባትዋ ፡ ከዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ አግብተዋት ፡ ፈረንሣዊ ፡ ተምራ ፡ ነበር ።

በኋላም ፡ ለትምህርት ፡ ፓሪስ ፡ ልኳት ፡ ሰንት ፡ ባርብ ፡ ከሚባል ፡ ኰሌጅ ፡ ገብታ ፡ ትምህርትዋን ፡ ስትቀጥል ፡ የፋሽሽት ፡ መሪ ፡

ሙሶሊኒ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመውረር ፡ በሚናገረው ፡ ዛቻ ፡ ምክንያት ፡ ተቋርጣ ፡ እንዳትቀር ፡ አባትዋ ፡ ወዳገርዋ ፡ መለሳት ።

ስለዚህ ፡ የትልልቅ ፡ ደራሲዎች ፡ የፈረንሣዊ ፡ መጻሕፍቶች ፡ ይዛ ፡ ስለመጣች ፡ አንዳንድ ፡ የመከራ ፡ ጓደኞችዋን ፡ መጻሕፍቶች ፡ ስትይዝ ፡ ወደ ፡ ውጪ ፡ አትሄድም ፡ ነበር ።

# ምዕራፍ ፡ ፪

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከየካቲት ፡ ፲፪ ፡ አደባባይ ፡ አጠገብ ፡ ካለው ፡ የሕዝብ ፡ አታክልት ፡ ውስጥ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ከአቃቂ ፡ መጥታ ፡ ከአንድ ፡ የድንጋይ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ተቀምጣ ፡ መጽሐፍ ፡ ስታነብ ፡ አንድ ፡ ወጣት ፡ ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ የሚባል ፡ የካብታም ፡ ልጅ ፡ በካዲላክ ፡ ኦቶሞቢል ፡ ራሱ ፡ እየነዳ ፡ ካታክልቱ ፡ ቅጥር ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ከኦቶሞቢሉ ፡ ወርዶ ፡ በእግሩ ፡ ሲናፈስ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍንን ፡ ከድንጋይ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ተቀምጣ ፡ መጽሐፍ ፡ ስታነብ ፡ አያት ።

በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በመልኳ ፡ ማማርና ፡ በውበቷ ፡ ግርማ ፡ ልቡ ፡ በፍቅር ፡ ተነክቶ ፡ ካጠገብዋ ፡ ከዚያው ፡ ከድንጋይ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ፡ ለማነጋገር ፡ ስለፈራ ፡ ልበል ፡ ልተው ፡ እያለ ፡ ካመነታ ፡ በኋላ ፡ በድፍረት ፡ ቃል ፡ እባክሽ ፡ ይቅር ፡ በይኝና ፡ ምን ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ፡ የምታነቢ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃት ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ አስቀድሞ ፡ መተዋወቅ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የማነበውን ፡ መጽሐፍ ፡ መጠየቅ ፡ ይገባ ፡ ነበር ። በምን ፡ መብትህ ፡ ነው ፡ ሳታውቀኝ ፡ የማነበውን ፡ መጽሐፍ ፡ የምትጠይቀኝ ፡ ብላ ፡ ተቆጣችው ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ይቅር ፡ በይኝ ፡ ብሎ ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡ በግሩ ፡ ባታክልቱ ፡ ውስጥ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ይል ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ ሁለቱም ፡ በዕድሜ ፡ የተመሳሰሉ ፡ ወጣቶች ፡ ስለሆኑ ፤ የሁለቱም ፡ ልብ ፡ በፍቅር ፡ ተነክቶ ፡ እሱ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ሲያያት ፡ እርስዋም ፡ ስታየው ፡ ዓይን ፡ ላይን ፡ ይጋጠሙ ፡ ነበር ።



ልጅ ፡ ዓስ ስታና ፡ ፀሐይ ፡ ስፍን ።

ሩብ ፡ ሰዓት ፡ እንደዚሁ ፡ በግሩ ፡ እየተናፈሰ ፡ ሲተያዩ ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ ሁለተኛ ፡ ተመልሶ ፡ ከዚያው ፡ ካጠገብዋ ፡ ከድንጋይ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ከኪሱ ፡ ጋዜጣ ፡ አውጥቶ ፡ ያነብ ፡ ጀመር ።

ነገር ፡ ግን ፡ ሁለቱም ፡ ሰርቀው ፡ ለማየት ፡ ሲዞሩ ፡ የሁለቱም ፡ ዓይን ፡ ይገናኝ ፡ ነበር ።

እንደበረሁም ፡ ዝም ፡ ብለህ ፡ ሲያ ቡ ፡ ጥቂት ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ስላሳፈርኩህ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ ያሳፈርኩህም ፡ ምክንያቴ ፡ እንዳንተ ፡ ያለ ፡ የተማረ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ልጅምን ፡ እንደሆንኩ ፡ ሳታውቀኝ ፡ ሳላውቅህ ፡ ምን ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ፡ የምታነቢው ፡ ብለህ ፡ ስለጠየቅኸኝ ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ ምንም ፡ ይቅርታ ፡ ባትጠይቀኝ ፡ ጥያቄህኝ ፡ ስለተቀበልሁ ፡ እነዚህ ፡ መጽሐፎቶች ፡ አንዱ ቪክቶሪጐ ፡ የሚ ባ ል ፡ የፈረንሣዊ ፡ ሊቅ ፡ የጻፈው ፡ ሚዜራብል ፡ የሚባል ፡ ጽሑፍ ፡ ነው ።

ሁለተኛው ፡ የድሆች ፡ ከተማ ፡ የሚባል ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰው ፡ የጻፈው ፡ ነው ፡ ብሳ ፡ ሰጠችው ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ተቀብሎ ፡ ጥቂት ፡ ከተመለከተው ፡ በኋላ ፡ እህቴ ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ ፈረንሣዊ ፡ አላህቅም ።

ነገር ፡ ግን ፡ ይህንን ፡ መጽሐፍ ፡ በእንግሊዝ ፡ ቋንቋ ፡ ተተርጉሞ ፡ ኣንብቤዋለሁ ፡ የድሆች ፡ ከተማንም ፡ ተመልክቸዋለሁ። ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ ስለምን ፡ እንዳንቺ ፡ ያለሽ ፡ ወጣት ፡ እንደዚህ ፡ ያሉትን ፡ መጻሕፍቶች ፡ የምትመለከቻቸው ፡ ምክንያቱም ፡ የወጣትነትሽን ፡ አሳብ ፡ በጣም ፡ ያደክምብሻል ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ በጣም ፡ የሚያሳዝኑ ፡ ጽሑፎች ፡ ናቸው ።

ነገር ፡ ግን ፡ ለእንደኔ ፡ ላለች ፡ ለኃዘን ፡ ለተፈጠረች ፡ ወጣት ፡ ሐዘንን ፡ እንደ ፡ ሚያቀሉ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

በሽታን ፡ በበሽታ ፡ ነው ፡ መከላከል ፡ የሚገባ ፡ ለምሳሌ ፡ ፈንጣጣን ፡ በፈንጣጣ ፡ ተስቦን ፡ በተስቦ ፡ መርዝን ፡ በመርዝ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ያዘነ ፡ ልብ ፡ በደስታ ፡ እንደ ፡ ማይሻር ፡ አታውቅምን?

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ እንዳልሺው ፡ ይሆን ፡ ይሆናል ።

ነገር ፡ ግን ፡ እንደኔ ፡ ሃሣብ ፡ የዓለምን ፡ ከባድ ፡ ሸክም ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ጥሎ ፡ እንደ ፡ ልጅ ፡ መሆን ፡ ያስፈልግ ፡ ይመስለኛል ።

ያለዚያ ፡ ግን ፡ ሰውነትን ፡ ማድከምንና ፡ አጥቁሮ ፡ ማየትን ፡ ከመፍጠሩም ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የመምሰል ፡ በሽታን ፡ ያመጣል ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ ሕሊናን ፡ ለመደለል ፡ የሚቻል ፡ ከሆነ ፡ እንደ ፡ ልጅ ፡ መሆን ፡ መልካም ፡ ነው ።

ነገር ፡ ግን ፡ ልብ ፡ ዋዛ ፡ አያውቅም ፡ ባይኖረኝ ፡ ነው ፡ አቅም ፡ እንደተባለው ፡ ሕሊናን ፡ ለመደለል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አቅም ፡ ካልተገኘ ፡ የሚቻል ፡ አይመስለኝም ፡

ልጅ ፡ ዓለመ ፡ እንግዲያስ ፡ ከሁሉም ፡ የሚበልጥ ፡ አሳብን ፡ ለማቅለል ፡ ጊዜን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ ያስፈልጋል ። ስለምን ፡ ሥራ ፡ ኣትሠሪም?

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ሥራ ፡ ማግኘትማ ፡ ኣንድ ፡ ዋና ፡ ዕድል ፡ እርሱ ፡ ኣልነበረምን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ትምህርቴ ፡ የፈረንሳዊ ፡ ቋንቋ ፡ ስለሆነ ፡ በብዙ ፡ ሥፍራ ፡ ሥራ ፡ ጠይቄ ፡ ትምህርትሽ ፡ በእንግሊዝ ፡ ቋንቋ ካልሆነ ፡ አንቀበልሽም ፡ ብለው ፡ መለሱኝ ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ይቅርታ ፡ አድርጊልኝና ፡ ይህንን ፡ የሚያሳዝን ፡ ጨዋታ ፡ ትተን ፡ ወደሌላ ፡ ጨዋታ ፡ እንመለስ ፤ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ የትውልድ ፡ አገርሽ ፡ ወዴት ፡ ነው?

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ አገሬ ፡ ሸዋ ፡ ነው ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ አባት ፡ እናት ፡ አሉሽን?

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ እናቴ ፡ አሁን ፡ በቅርብ ፡ ቀን ፡ ሞተች ፡ አባቴ ፡ ግን ፡ በ፲፱፻፳፰ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በተደረገው ፡ ጦርነት ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ሞተ

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ካባትሽ ፡ ብዙ ፡ ካብት ፡ አላገኘሽምን?

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ አባቴ ፡ ፊትም ፡ ቢሆን ፡ ብዙ ፡ ካብት ፡ የለውም ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ በመጠነኛ ፡ ኑሮ ፡ ለመኖር ፡ የሚበቃ ፡ ገንዘብ ፡ ነበረው።

በጠላት ፡ ወረራ ፡ ጊዜ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ስለሀገሩ ፡ በአርበኝነት ፡ በመሞቱ ፡ ጠላት ፡ እንደ ፡ ከሃዲ ፡ ቆጥሮት ፡ በፋሺሽት ፡ ሕግ ፡ ተወርሶ ፡ በከተማ ፡ ቦታውም ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ትልልቅ ፡ ቤቶች ፡ ተሠርተውበት ፡ ስል ፡ ነበረ ፡ መንግሥታችን ፡ ከተመለሰ ፡ ወዲህ ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ የቤቱን ፡ ግምት ፡ ለመክፈል ፡ ስላልቻልኩ ፡ የቦታውን ፡ ግምት ፡ ብቻ ፡ ተቀብዬ ፡ ያባቴን ፡ ርስት ፡ ለቀቅሁ ።

ልጅ ፡ ዓለም ፡ ደስታ ፡ አባትሽ ፡ ያያት ፡ የቅድመኝ ደጅ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ርች ፡ ጉልት ፡ የለውምን?

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ጥያቄ ፡ ስለጠየቅሽኝ ፡ በጣም ፡ አመሰግንሃለሁ ፡ የኔ ፡ ቅድማያቶችና ፡ አያቶች ፡ ባለፈው ፡ አራትና ፡ አምስት ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ ስም ፡ ጥሩ ፡ መሳፍንቶችና ፡ አቅኚዎች ፡ ነበሩ ።

እንደዚሁ ፡ ቅድማያቶቼ ፡ ካብታቸው ፡ ጦርና ። ጋሻ ፡ ፈረስና ፡ ወታደር ፡ ነበር ። መሬትና ፡ ገንዘብ ፡ ለነሱ ፡ ምናቸውም ፡ አልነበረም ። ርስት ፡ ጉልታቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነጻነት ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ በዚሁ ፡ ደስ ፡ ብሎዋቸው ፡ ለራሳቸው ፡ ጥቅም ፡ ሳያስቡ ፡ ዘመናቸውን ፡ አሳለፉት ።

ነገር ፡ ግን ፡ አዲሱ ፡ ዘመን ፡ ባባቴ ፡ ላይ ፡ ሲደርስ ፡ የዘመኑ ፡ ደስታ ፡ መሬት ፡ ማግኘትና ፡ ብዙ ፡

ገንዘብ ፡ መሰብሰብ ፡ ስለሆነ ፡ ዘር ፡ ከልጉዋም ፡ ይንል ፡ እንደቶባታው ፡ አባቴ ፡ ኩራቱንና ፡ ሕሊናውን ፡ ጥሎ ፡ ገንዘብ ፡ ዝመፈለግ ፡ ውርደት ፡ ስለመሰሰ ፡ በመጠነኛ ፡ ኑሮ ፡ አቅሙን ፡ አውቆ ፡ መኖር ፡ ስለቆረጠ ፡ ብዙ ፡ ካብት ፡ አልነበረውም ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ተከዞ ፡ በሁለት ፡ እጁ ፡ እንጨን ፡ ይዞ ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ ያይ ፡ ነበር ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ጊዜያችንን ፡ በኃዘን ፡ ከማሳለፍ ፡ እስቲ ፡ ፍቀድልኝና ፡ አንተን ፡ ልጠይቅህ?

ልጅ ፡ ዓይኑ ፡ ደስታ ፡ እሺ ፡ በጣም ፡ ደስ ። ይለኛል ፡ ጠይቂኝ ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ የትውልድ ፡ አገርህ ፡ ወዴት ፡ ነው?

ልጅ ፡ ዓለም ፡ ደስታ ፡ ከዚህ ፡ አዲስ ፡ አበባ ነው ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ አባት ፡ እናት ፡ ኣሉህን?

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ አባቴ ፡ አሁን ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ሞትዋል ። እናቴ ፡ ግን ፡ አለች ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ካባትህ ፡ ብዙ ፡ ከቶ ፡ አልገኘ ምን?

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ በጣም ፡ ልክ ፡ ያለፈ ፡ ካብት ፡ ትቶልኛል ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ይህንን ፡ ካብት ፡ አባትህ ፡ ካያት ፡ ከቅድማያቱ ፡ ያገኘው ፡ ነውን?

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ያባቴ ፡ አያቶቹና ፡ ቅድማያቶቹ ፡ ካብት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ቋንቋውንም ፡ አያውቁት ፡

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ እንግዲያስ ፡ እንደምን ፡ ከበረ?

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ አባቴ ፡ ዶሮና ፡ እንቁላል ፡ ቅመማ ፡ ቅመም ፡ ሸጭ ፡ ነጋዴ ፡ ነበር ። ጠላት ፡ አገራችን ፡ ሲገባ ፡ ለፋሺሽቶች ፡ ዶሮና ፡ እንቁላል ፡ በመሸጥ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አገኘ ።

ይልቁንም ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከኢጣሊያን ፡ ሹማምንቶች ፡ በመተዋወቁ ፡ ጨውና ፡ አቡጀዲ ፡ በርካሽ ፡ እየገዛ ፡ እንዲቸረችር ፡ ፈቀዱለትና ፡ ብዙ ፡ ገንብ ፡ አገኘ ፡

ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቸርነቱ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነፃነት ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥታችን ፡ ይዘውልን ፡ ሲመጡ ፡ ብዙ ፡ አርበኞችና ፡ ስደተኞች ፡ አብረው ፡ ስለገቡ ፡ አባቴ ፡ በጣም ፡ መተዳደርና ፡ መለማመጥ ፡ ስለሚያውቅ ፤ እነሱን ፡ በገንዘብ ፡ በመርዳትና ፡ ንግድና ፡ ጥቅም ፡ በማሳየት ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አገኘ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ብዙ ፡ ርስትና ፡ ቤት ፡ አለውን?

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ብዙ ፡ መሬት ፡ እንኳን ፡ የለውም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የሚከራዩ ፡ ሱቆችና ፡ ቤቶች ፡ ብዙ ፡ አሉት ። ይልቁንም ፡ ካብቱ ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ነው ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ሰዓትዋን ፡ አይታ ፡ ወንድሜ ፡ ቀጠሮ ፡ ስላለኝ ፡ እንግዲህ ፡ ልሂድ ፡ ፍቀድልኝ ፡ አለችው ፡

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ምነው ፡ ዋናውን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ሳንጫወት ፡ ትሔጃለሽ ፡

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ምን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ጫወታ ፡ አለን ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ቤትሽ ፡ ወዴት ፡ ነው

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ከዚሁ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ባል ፡ አግብተሻልን?

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ገና ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ ያልሞላኝ ፡ ወጣት ፡ እንደምን ፡ ባል ፡ አገባለሁ ፡

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ እንግዲያው ፡ ልጅም ፡ የለሽ ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ከት ፡ ብላ ፡ ስቃ ፡ ከባል ፡ በፊት ፡ ልጅ ፡ ይስጥሽ ፡ የተባለው ፡ ተረት ፡ ደረሰ ።

እንደምን ፡ ባል ፡ ሳላገባ ፡ ልጅ ፡ እወልዳለሁ?

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ይቅር ፡ በይኝ ፡ ወጃጁ ፡ ልብስሽ ፡ አራስ ፡ አራስ ፡ ስለ ፡ ሸተተኝ ፡ ነው ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ አንዲት ፡ የምወዳት ፡ ጕረቤቴ ፡ በጣም ፡ የምታምር ፡ ልጅ ፡ ስላላት ፡ እሰዋን ፡ ታቅፌ ፡ ነው ፡ የምውል ፡ ስለዚህ ፡ ልብሴ ፡ ሸትቶህ ፡ ይሆናል ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ እንግዲህ ፡ ወዳጄ ፡ ደፈርከኝ ፡ አትበይኝና ፡ በጣም ፡ ወድጄሻለሁ ፡ እንጋባ

በሐይ ፡ መስፍን ፡ አንተን ፡ ማግባት ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ይለኝ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ተገናኝተን ፡ ወዲያው ፡ ቃሌን ፡ ከ መስጠት ፡ ያሳፍራል ። እባክህ ፡ ወዳጄ ፡ ወዴት ፡ ጋር ፡ ነው ፡ የተማርከው?

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ አሜሪካን ፡ አገር ፡ ሎምቦ ፡ ከሚባል ፡ ዩኒቬርሲቲ ፡ የመሐንዲስ ፡ ትምህርቴን ፡ ጨርሼ ፡ ዲግሪዬኝ ፡ ተቀብዬ ፡ መጣሁ ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ሳቅ ፡ ብላ ፡ እንግዲህ ፡ በውነት ፡ የዚህ ፡ አሳብ ፡ ካለህ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንፈላለግ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ልሒድ ፡ አለችው ።

ልጅ ፡ ዓለማው ፡ ደስታ ፡ እንግዲያው ፡ መቼ ፡ እንገናኝ ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ተነገ ፡ ወዲያ ፡ ከኩለ ፡ ቀን በኋላ ፡ በ፲ ፡ ሰዓት ፡ ከዚህ ፡ ድረስ ፡ እንገናኝ ፡ ተባብለው ፡ ሁለቱም ፡ ወደየቤታቸው ፡ ሔዱ ።

# ምዕራፍ ፡ ፫ ፡

ልጅ ፡ ዓለም ፡ ደስታም ፡ በኦቶሞቢሉ ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ በረረ ።

ፀሐይ ፡ መስፍንም ፡ ኦቶቡስዋን ፡ ይዛ ፡ ወደ ፡ አቃቂ ፡ በሰቃ ፡ ጐጆዋ ፡ ሔደች ።

ነገር ፡ ግን ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ከዚያች ፡ ከድሀ ፡ ጐጆዋ ፡ ገብታ ፡ ሦስቱም ፡ ልጆችዋ ፡ አንገትዋ ፡ ላይ ፡ ተጠምጥመው ፡ ሲስምዋት ፡ ዕንባዋ ፡ እንደ ፡ ጐርፍ ፡ ይፈስ ፡ ነበር ። ምክንያቱም ፡ ኑሮዋ ፡ የተሻሻለላት ፡ መስልዋት ፡ ልጃገረድ ፡ አይደለችም ፡ ብሎ ፡ እንዳይተዋት ፡ ልጆችም ፡ የሉኝ ፡ ብላ ፡ ስለካደቻቸው ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ድሀ ፡ በሕልሙ ፡ ቅቤ ፡ ባይጠጣ ፡ ንጣት ፡ ይገድለው ፡ ነበር ፡ እንደተባለው ፡ ያ ፡ የካብታም ፡ ልጅ ፡ በሰጣት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አምና ፡ ቅዳሜ ፡ እስኪ ፡ ደርስ ፡ ድረስ ፡ እንቅልፍ ፡ አልተኛችም ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዚያው ፡ በቀጠሮው ፡ የካቲት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ መታሰቢያ ፡ አጠገብ ፡ ካለው ፡ የሕዝብ ፡ አታክልት ፡ ውስጥ ፡ ቀድማ ፡ ቆየችው ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ከጐረቤት ፡ ልብስ ፡ ተውሳ ፡ ታጥባ ፡ ሽቶ ፡ ተቀብታ ፡ በጣም ፡ አምራ ፡ ስለመጣች ፡ ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ በሩቅ ፡ አይትዋት ፡ በኦቶመቢሉ ፡ እየበረረ ፡ መጥቶ ፡ የኔ ፡ ወዳጅ ፡ ደህና ፡ መጣሽልኝ ፡ ብሎ ፡ እቅፍ ፡ አድርጐ ፡ ከሳማት ፡ በኋላ ፡ ከድንጋይ ፡ ወንበሩ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ይጫወቱ ፡ ጀመር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ወዳጄ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ካንቺ ፡ ከተለያየን ፡ የጋብቻችንን ፡ ነገር ፡ ሳወጣ ፡ ሳወርድ ፡ ከቆየሁ ፡ በኋላ ፡ እኔ ፡ በዚሁ ፡ ቆረጥሁ ፡ አንቺ ፡ ምን ፡ አሰብሽ?



አቃቂ ፡ የሚሔድ ፡ የኦቶብስ ፡ ጣቢያ ፡

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ እኔም ፡ ብሆን ፡ መጋባታችን ፡ ደስ ፡ ይለኝ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በችኰላ ፡ ስለሆነ ፡ ፈራሁ ። ባገራችን ፡ ምሳሌ ፡ ሲሮጡ ፡ የታጠቁት ፡ ሲሮጡ ፡ ይፈታል ። እንደተባለው ፡ እንዳይሆን ፡ ያሰጋል ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ የችኰላና ፡ የወረት ፡ ነገር ፡ አይምሰልሽ ፡ ወዳጄ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ብዙ ፡ ልጃገረዶች ፡ ብዙ ፡ ወጣቶች ፡ ትምህርታቸውን ፡ እየጨረሱ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ የመጡ ፡ ለኔ ፡ ጓደኛ ፡ ለመሆን ፡ እኔን ፡ ለማግባት ፡ ደክመው ፡ ነበር ። ምንም ፡ ፍቅራቸው ፡ አልሳበኝም ።

ነገር ፡ ግን ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ያለኝ ፡ የፍቅር ፡ ስሜት ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ለንደዚህ ፡ ያለ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ጉዳይ ፡ ቀን ፡ አንስጠው።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ የኔ ፡ ወዳጅ ፡ ፍቅር ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ጠባዮች ፡ አሉት ። አንደኛው ፡ መሠረታዊ ፡ ሁለተኛው ፡ ተላላፊ ፡ ነው ። መረታዊው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ልብን ፡ ካቆሰስ ፡ በምንም ፡ አኳኋን ፡ መለያየት ፡ አይቻልም ። ተላላፊው ፡ ፍቅር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ገለባ ፡ እሳት ፡ ብው ፡ ብሎ ፡ ይነድና ፡ ወዲያው ፡ ይጠፋል

ስለዚህ ፡ የትኛው ፡ መሆኑን ፡ ስላላወቅሁት ፡ እምነት ፡ የለኝም ።


ወንድሜ ፡ ሆይ ፍቅር ፡ እንደ ፡ አሞራ ፡ በክንፉ ፡ የሚበር ፡ ስሌሆነ ፡ በሚያርፍበት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ዓለምንና ፡ የስታን ፡ ወይም ፡ የሚያስገርም ፡ *ከራ ፡ ስለሚጥራ ፡ ብዙ ፡ የሚያሰጋ ፡ በመሆኑ ፡ ማሰብና ፡ መጠንቀቅ ፡ ያስፈልጋ ል ፡ በማለት ፡ ነው ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ ስለምንድነው ፡ ዘውትር ፡ አጥቁረሽ ፡ የምታይ ፡ ፍቅር ፡ ፍቅር ፡ ነህ ፡ ጋብቻም ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አይደለም ።

እኔ ፡ እንደ ፡ ወደድኩሽ ፡ አንቺም ፡ ወደሽኝ ፡ እንደሆነ ፡ እንጋባ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ካለ ፡ ደን ፡ ውስጥ ፡ በጨለማ ፡ ጋብተሽ ፡ ለምን ፡ በሐሳብ ፡ ትጨነቂያለሽ ፡

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ መልክ ፡ ስለ ፡ ተፈጠረ ፡ እንደ ፡ ከበት ፡ አለም ፡ ሣር ፡ በማየት ፡ ወደ ፡ ገደል ፡ አይገባም። መኝ ናቸውንም ፡ ነገር ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ማየት ፡ ኡስበት ። ስለዚህ ፡ ድጄሃለሁ ፡ በድጄ ሻለሁ ፡ ተባብለን ፡ ጥቂት ፡ ሳናስብበት ፡ ጋብቻን ፡ ያህል ፡ ነገር ፡ አሁን ፡ ልንቆርጠው ፡ አይቻልም ፡ ማለት ፡ ነው ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ተይው ፡ የኔ ፡ ወዳጅ ፡ ኣወቅሁት ፡ አንዳንድ ፡ ሴቶች ፡ የመምሰል ፡ በሽታ ፡ ስላለባቸው ፡ አጥቁረው ፡ የሚያዩት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የውነት ፡ እየመሰላቸው ፡ እንዳዘኑ ፡ ይኖራሉ ። ከዚህ ፡ ሃሣብ ፡ ውስጥ ፡ ለመውጣት ፡ ምናልባት ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ በኡቶመቢል ፡ መንፈስ ፡ ይሻል ፡ እኔደያኔ ። ትንሽ ፡ ንፋስ ፡ እንቀበል ።



በነፃነት ፡ ሐውልት ፡ በኩል ፡ ሲያልፉ ፡

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ከት ፡ ብላ ፡ ስቃ ፡ አሳቤን ፡ እኔው ፡ ይሄው ፡ ስለምሔድ ፡ በመናፈሳችን ፡ ምን ፡ ይለወጥ ፡ መስሎህ ፡ ነው ፡ ብላው ፡ ለመሔድ ፡ ተነስተው ፡ ከአቶመቢላቸው ፡ ሳይ ፡ ተቀምጠው ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጐዳና ፡ ገብተው ፡ ወደ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሐውልት ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ሲደርሱ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ ይህ ፡ ከፊለፊታችን ፡ ያለው ፡ ሦስት ፡ ፎቅ ፡ ትልቅ ፡ ቤት ፡ የማን ፡ ቤት ፡ ነው ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ የኔ ፡ ነው ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ያያት ፡ የቅድም ፡ አያትህ ፡ ርስት ፡ ነውን?

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ እቅፍ ፡ አድርጐ ፡ ስሞ ፡ ምነው ፡ የኔ ፡ ወዳጅ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ አልነገርኩሽምን ፡ ላባቴ ፡ አያቱና ፡ ቅድማያቱ

፡ ጊዜ ፡ ነው ። የኢትዮጵያ ፡ ጥፋት ፡ ላባቴ ፡ ልማት ፡ ሆኖት ፡ በዶሮና ፡ በንቁላል ፡ ያገኘው ፡ ካብት ፡ ነው ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ እባክህ ፡ ወዳጄ ፡ አባትህ ፡ ይህነን ፡ የሚያህል ፡ ቤት ፡ ገዛው ፡ ወይስ ፡ ሥራው?

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ይህ ፡ ቦታና ፡ ቤት ፡ ያንድ ፡ ትልቅ ፡ መስፍን ፡ ርስት ፡ ነበር ፡ በዕዳ ፡ ምክንያት ፡ ሐራጅ ፡ ሲባል ፡ የኔ ፡ አባት ፡ ገዛው ።


ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ እባክህ ፡ ወንድሜ ፡ ይህነን ፡ ያህል ፡ ርስት ፡ ሐራጅ ፡ ሲባል ፡ ለማዳንና ፡ ለመከላከል ፡ መስፍኑ ፡ ወገን ፡ የለውም ፡ ነበርን?

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ብዙ ፡ ወገኖችስ ፡ ነበሩት ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ የሚደርስ ፡ ስላልመሰላቸው ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ተደንቀው ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ በመፍረድ ፡ ዝም ፡ ስላሉ ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ቤተሰቦች ፡ ሁሉ ፡ እንደዚሁ ፡ እየሟሙ ፡ ያለቁ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ዓይንዋን ፡ በመሐረብ ፡ ይዛ ፡ ስቅቅ ፡ ብላ ፡ አለቀሰች ፡

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ምነው ፡ የኔ ፡ ወዳጅ ፡ ለምን ፡ ታለቅሻለሽ?

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ የኔ ፡ አባት ፡ አኳኋን ፡ ትዝ ፡ ብሎኝ ፡ ነው ፡ ምክንያቱም ፡ አባቴ ፡ አንዳንድ ፡ ቀን ፡ ተክዞ ፡ ከወንበር ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ እያዘነ ፡



የአቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሐውልት ፡

ጊዜ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ቁም ፡ ነገራም ።

ባላባትነት ፡ አያኮራም ።

ገዝተው ፡ እንዲያው ፡ አይሔዱም ።

ድላል ፡ አለ ፡ አሉ ፡ በምድርም ፡ እያለ ፡ ያንጐራጕር ፡ ነበር ።

ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ የትውልድ ፡ ዛፍ ፡ አድጐ ፡ ወፍሮ ፡ ረዝሞ ፡ ቅርንጫፉና ፡ ቅጠሉ ፡ ሰፍቶ ፡ ለሰውም ፡ ለእንስሳም ፡ ጥላ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ጊዜ ፡ ግርሶ ፡ እንደሚጥለው ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡ ከደስታዬ ፡ ይልቅ ፡ ኃዘኔ ፡ የሚያመዝነው ፡ አንተም ፡ ዘወትር ፡ ሰምን ፡ አጥቁረሽ ፡ ታያለሽ ፡ ብለህ ፡ የምትቆጣኝ ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ እንግዲህ ፡ አንቺን ፡ ደስ ፡ የሚልሽ ፡ ነገር ፡ ከሌለ ፡ ምናልባት ፡ የደስታ ፡ አጠፌታውን ፡ እንደሆነ ፡ የምትወጂው ፡ ጉለሌ ፡ እንሒድና ፡ ከፈረንጆች ፡ መቃብር ፡ አታክልት ፡ ውስጥ ፡ እንናፈስ ፡ አላት ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ወንድሜ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ ምክንያቱም ፡ በሽታን ፡ በበሽታው ፡ ሲያክሙት ፡ ነው ፡ የሚድነው ፡ ብዬ ፡ እንደነገርኩህ ፡ የኔንኃዘን ፡ በኃዘን ፡ ቢያክሙኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የምድን ፡ በደስታ ፡ አይደለም ።

የኔ ፡ ወዳጅ ፡ የኔን ፡ ኃዘን ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ደግፎ ፡ የያዘኝ ፡ ይህ ፡ በጄ ፡ ያለው ፡ ሚዝራብል ፡ የሚባል ፡ የቪክቶሪጉ ፡ መጽሐፍና ፡ የድሆች ፡ ከተማ ፡ የሚባሉት ፡ ናቸው ።

ከዚህም ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የበረዝ ፡ የሚያጽናናኝ ፡ ኰዚት ፡ ከምትባል ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ የደረሰባትን ፡ መከራ ፡ ሳነብ ፡ ነው ፡ አለችው።

# ምዕራፍ ፡ ፬ ፡

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታም ፡ እንግዲያው ፡ እንሒድ ፡ ብሎ ፡ በካዲላክ ፡ ኦቶሞቢል ፡ ይዝዋት ፡ ወይደ ፡ ጉለሌ ፡ በረረ ።

ከኦቶቢሉም ፡ ወርደው ፡ ከመቃብር ፡ አታክልት ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ በእግራቸው ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ የሙታንን ፡ ሐውልቶች ፡ እየተመለከቱ ፡ ይናፈሱ ፡ ነበር ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ የኔ ፡ ወዳጅ ፡ ሰውን ፡ ያህል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ፍጥረት ፡ እንደዚህ ፡ ማዋረድ ፡ አይገባሽም ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ሳቅ ፡ ብላ ፡ ከዓለም ፡ ጋር ፡ አዲስ ፡ ወዳጅ ፡ በመሆንህ ፡ የዓለምን ፡ ከንቱነት ፡ የሰውን ፡ ጥፋት ፡ ገና ፡ ለምን ሰብ ፡ አልቻልከም ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ወዳጄ ሆይ በዓለም ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡ ወገን ፡ ተከራካሪዎች ፡ እንዳሉ ፡ የታወቀ ፡ ነው። አንዱ ፡ በስንፍናው ፡ ከዓለም ፡ ዕድል ፡ ውጪ ፡ በመሆኑ ፡ ዓለምን ፡ ከንቱ ፡ ናት ፡ በማለት ፡ ድህነቱንና ፡ ችግሩን ፡ ይጽናናበታል ። ሁለተኛው ፡ ዕድል ፡ መርጣ ፡ ከዓለም ፡ ስላስተዋወቀችው ፡ ራሱም ፡ ጠቅሞ ፡ ወገኑንም ፡ ጠቅሞ ፡ በመኖሩ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ይኖራል ። ሁሉም ፡ መጨረሻቸው ፡ ያው ፡ መቃብር ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ እስከዚያው ፡ ድረስ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ቢሞት ፡ አይሻል ፡ ምን?

እህቴ ፡ ሆይ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ የእውቀቱን ፡ ብርሃን ፡ በዕቃ ፡ ውስጥ ፡ ሸፍኖ ፡ ማስቀመጥ ፡ በወንጌልም ፡ ክልክል ፡ ነው ።

መድኃኒታችንም ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ የተሠራ ፡ ቤት ፡ መሠወር ፡ አይችልም ፡ እንዳሰው ፡ የሰውን ፡ ልጆች ፡ እውቀትና ፡ ብልጠት ፡ ትጋት ፡ በሥራም ፡ መፍጨርጨርን ፡ የሚከለክል ፡ መጽሐፍና ፡ ፍልስፍና ፡ የለም ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ እንደምትለው ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ ይገባኛል ፡ በብልጠትና ፡ በትጋት ፡ ተፍጨርጭረው ፡ ደክመው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብርና ፡ ከብትም ፡ ቢያገኙ ፡ በጊዜ ፡ ምክንያት ፡ የዕድላቸው ፡ አበባ ፡ ገርጥቶ ፡ ከመጨረሻ ፡ ችግር ፡ ስለሚወድቁ ፡ በዕድልና ፡ በካብት ፡ በብልጠትና ፡ በትጋት ፡ መመካት ፡ አያስፈልግም ፡ ለማለት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ዓለም ፡ ወረተኛ ፡ መሆንዋን ፡ ከመጽሐፍ ፡ አላነበብክምን ። ሲጠልዋት ፡ የምትቀርብ ፡ ሲወዱዋት ፡ የምትርቅ ፡ አመለቢስ ፡ ቀብራራ ፡ መሆንዋን ፡ አታውቅምን ፡ ዓለም ፡ ዛሬ ፡ ወዳጅ ፡ ነገ ፡ ጠላት ፡ ስለሆነች ፡ እምነት ፡ አይጣልባትም ፡ እንግዲህ ፡ ይህንን ፡ የመረረ ፡ ጫወታ ፡ እንተውና ፡ የሙታን ፡ መታሰቢያዎችን ፡ እየተናፈስን ፡ እንመልከት ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ እሺ ፡ በእግራችን ፡ እንሂድ ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ የዚህ ፡ የሽማግሌ ፡ ሐውልት ፡ እንደምን ፡ ደስ ፡ ይላል ። ከሥሩም ፡ የተጻፈው ፡ የሕይወቱ ፡ ታሪክ ፡ ያኮራል ። ዕድሜውም ፡ በሰማንያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ስለሞተ ፡ መልካም ፡ እድሜ ፡ ጠግቦ ፡ አንቀላፍትዋል ። ብላ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ሐውልት ፡ እጅ ፡ እጅ ፡ ተያይዘው ፡ ሲሔዱ ፡ ብዙ ፡ ሐውልቶች ፡ እያዩ ፡ ካለፉ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ አንድ ፡ የሕፃን ፡ ልጅ ፡ ሐውልት ፡ በዕብነ ፡ በረድ ፡ የተሠራ ፡ አይታ ፡ ቆማ ፡ ጠጋ ፡ ብላ ፡ ጽሕፈቱን ፡ ስትመለከት ፡ በ፫ ፡ ዓመቱ ፡ በአደጋ ፡ ምክንያት ፡ የሞተ ፡ መሆኑን ፡ አንብባ ፡ ታለቅስ ፡ ጀመር ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ እንግዲህ ፡ መቼ ፡ ይሆን ፡ ደስ ፡ የሚልሽ ፡ የዚህን ፡ የህፃን ፡ ሐውልት ፡ በማየት ፡ ምን ፡ የሚያስለቅስ ፡ ነገር ፡ አገኘሽ ፡ ልጅ ፡ ቢኖርሽ ፡ እንኳ ፡ በልጁ ፡ ይደርሳል ፡ ብለሽ ፡ ብታለቅሺ ፡ ምክንያት ፡ አለሽ ፡ ኣንቺ ፡ ወጣት ፡ ልጃገረድ ፡ ነኝ ፡ ብለሽኝ ፡ ነበር ። የነገርሽኝ ፡ ኣሰት ፡ ነውን ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ እኔስ ፡ እንደነገርኩህ ፡ ልጃገረድ ፡ ነኝ ፡ ልጅም ፡ የለኝም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አንተ ፡ ሁለተኛ ፡ ይህነን ፡ የምታነሳብኝ ፡ የድህ ፡ በሽታው ፡ መዋሸት ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነውን?


ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ አይደለም ፡ እህቴ ፡ ልጅ ፡ እንደሌለሽ ፡ አምናለሁ ። ብቻ ፡ ለደስታችን ፡ እንቅፋት ፡ እንዲሆን ፡ የዚህን ፡ የህፃን ፡ ልጅ ፡ ሐውልት ፡ አይተሽ ፡ ስታለቅሺ ፡ ጊዜ ፡ ተቆጥቼ ፡ ነው ። አሁንስ ፡ እንሒድና ፡ ቤቴን ፡ በውጨ ፡ ላሳይሽ ፡ ነገ ፡ ማታ ፡ በሁለት ፡ ሰዓት ፡ እንድትመጪና ፡ ከናቴ ፡ ጋር ፡ ሦስታችን ፡ ብቻ ፡ ራታችንን ፡ በልተን ፡ የጋብቻችንን ፡ ፕሮግራም ፡ እናሰናዳለን ፡ አላት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታና ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ በኦቶሞቢላቸው ፡ ተቀምጠው ፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ሔዱ ። ከውጪ ፡ በኦቶመቢል ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ በጣቱ ፡ እያመለከቱ ፡ ይህ ፡ በፊት ፡ ለፊት ፡ የምታይው ፡ ሦስት ፡ ደርብ ፡ ቤት ፡ የመኖሪያችን ፡ ቤት ፡ ነው ። ከሱ ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ ነጭ ፡ ቤት ፡ የብዙ ፡ ሰው ፡ መኖሪያ ፡ ያለው ፡ እሱም ፡ የኔ ፡ ቤት ፡ ነው ።

ነገር ፡ ግን ፡ ለሁለት ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ በወር ፡ አከራይቼዋለሁ ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ይህ ፡ ሦስት ፡ ደርብ ፡ ቤት ፡ ለመኖሪያ ፡ አይበዛብህምን?

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ አይበዛብንም ፡ የታችኛው ፡ የምድር ፡ ቤቱ ፡ የኔ ፡ ቢሮና ፡ የእንግዳ ፡ መቀበያ ፡ እልፍኝና ፡ ሳሎን ፡ የሙብል ፡ ቤት ፡ አለው ። ከዚያ ፡ ቀጥሎ ፡ እናቴ ፡ ከሰው ፡ የምትገናኝበት ፡ ክፍል ፡ አለ ።



የልጅ ፡ ዓለመ ፡ ደስታ ፡ የመኖሪያ ፡ ቤት ።

በሁለተኛው ፡ ደርብ ፡ የናቴና ፡ የኔ ፡ መኝታ ፡ ቤትና ፡ ሳሉን ፡ ቢሮ ፡ ሁለት ፡ የመታጠቢያ ፡ ቤት ፡ ኣለው ።

ሦስተኛው ፡ ደርብ ፡ ግን ፡ ያሽከሮች ፡ ቤት ፡ ፀሐይ ፡ መሥፍን ፡ ይህንን ፡ ሁሉ ፡ ቤት ፡ ኣባትህ ፡ ነውን ፡ የሠራው ፡

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ የኔን ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ቦታውን ፡ ገዝቶ ፡ አባቴ ፡ የሠራው ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ትልቁን ፡ ቤት ፡ ካንድ ፡ አባቱ ፡ ከሞተበት ፡ ልጅ ፡ በወለድ ፡ ግድ ፡ ገንዘብ ፡ ኣበድሮት ፡ ለመክፈል ፡ ስላልቻለ ፡ ስለ ፡ ዕዳው ፡ የወሰደበት ፡ ነው ።

ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ የኔ ፡ አባት ፡ በጣም ፡ ደግ ፡ ሰወ ፡ ስለሆኔ ። በወለድ ፡ አግድ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ገንብ ፡ ቢለምነው ፡ አይከለክልም ፡ ነበር ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ከዓይንዋ ፡ እንባዋ ፡ እየፈሰሰ ፡ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ ያንተ ፡ አባት ፡ ዓሣ ፡ ለመያዝ ፡ በመንጠቆው ፡ ላይ ፡ ሥጋ ፡ ሰክቶ ፡ እንደሚያጠምድ ፡ ዓሣ ፡ ወጋሪ ፡ ነው ። እባክህ ፡ የኔ ፡ ወዳጅ ፡ አባቴ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ትቶልኛል ፡ የምትለው ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ካብት ፡ ነጩን ፡ እባክህ ፡ ለዚህ ፡ ለድሀ ፡ ገንዘቡን ፡ ይመልስልህና ፡ ርስቱን ፡ መልስለት ፡ እያለች ፡ ትለምነው ፡ ጀመር ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ወዴት ፡ አግኝቼው ፡ ነው ፡ የምመልስለት ፡ ያንን ፡ ገንዘብ ፡ ካባቴ ፡ ከወሰደ ፡ ወዲያ ፡ ኦቶመቢል ፡ ገዝቶ ፡ ሲናፈስ ፡ ካመንዝራዎች ፡ ጋር ፡ ሲበላ ፡ ሲጠጣ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ ወሬውን ፡ ብጠይቅ ፡ ገንዘቡ ፡ አልቆበት ፡ በችግርና ፡ በመከራ ፡ ምክንያት ፡ የሳምባ ፡ በሽታ ፡ ታሞሞተ ። የሚሉ ፡ ሰማሁ ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ አባትህና ፡ አንተ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዮች ፡ ናችሁ ። በተንኰል ፡ የተሰበሰበ ፡ ገንዘብ ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ ባሸዋ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ቤት ፡ ስለሆነ ፡ ምንም ፡ ደስ ፡ አያሰኝም ፡

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ገንዘብ ፡ ከወዴት ፡ ይመጣ ፡ ይመስልሻል ፡ እጅን ፡ አጣምሮ ፡ ገንዘብ ፡ ገንዘብ ፡ ቢሉት ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ኅብስተ ፡ መና ፡ ከሰማይ ፡ ይወርድ ፡ ይመስልሻልን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ዕድል ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ካርታ ፡ ጫወታ ፡ ነው ። አንዱ ፡ ያገኛል ፡ ሌላውም ፡ ያጣል። ያለዚያ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ ካብቱ ፡ ሳይነካ ፡ እንደያዘ ፡ ላዘለም ፡ የሚኖር ፡ ቢሆን ፡ ዘወትር ፡ እግዚአብሔር ፡ አዲስ ፡ ዓለም ፡

ሲፈጥር ፡ ይኖር ፡ ነበር ። እባክሽ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ አትዘኝ ፡ ይህ ፡ የመለኮት ፡ ዋናው ፡ ምሥጢራዊ ፡ ሥራው ፡ ነው ። ይልቁንስ ፡ የነገን ፡ ቀጠሮ ፡ እንዳትረሽ ፡ ብልዋት ፡ በቀጠሮው ፡ ተስማምተው ፡ ወደ ፡ አቃቂ ፡ በሰቃ ፡ በኦቶቡስ ፡ ላይ ፡ ተሳፍራ ፡ ሔደች ። በእጅዋ ፡ የያዘችውን ፡ ሚዜራብል ፡ የሚባል ፡ መጽሐፍ ፡ እያነበበች ፡ በዕድሌ ፡ ምክንያት ፡ ይህም ፡



በወለድ ፡ አግድ ፡ የተወሰደው ፡ ቤት ።

ያሰብነው ፡ ጉዳይ ፡ ይፈጸም ፡ ኣይመስለኝም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ዕድል ፡ ካዘነበለና ፡ የዕድሉ ፡ አበባ ፡ ከገረጣ ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ ኣይቃናም ። እያለች ፡ ስታስብ ፡ ከመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ምዕራፍ ፡ የዋቴርሎ ፡ ጦርነት ፡ ስለነበረ ፡ የናፖሊዎን ፡ አወዳደቅና ፡ የዕድሉ ፡ አበባ እንደምን ፡ እንደ ፡ ገረጣ ፡ ካነበበች ፡ በኋላ ፡ ሰሎሞን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ያው ፡ ተመልሶ ፡ ይደረጋል ፡ ያለው ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ እያለች ፡ በአሳብ ፡ ተውጣ ፡ ሳታውቀው ፡ ከቤቱዋ ፡ ደረሰች ፡

ከዚያም ፡ ከኦቶብስ ፡ ላይ ፡ ወርዳ ፡ ወደ ፡ ቤትዋ ፡ ገባች ።

ልጆችዋም ፡ እየተሯሯጡ ፡ መጥተው ፡ አንገትዋን ፡ አቅፈው ፡ ይስምዋት ፡ ጀመር

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ልጆችዋን ፡ በተራ ፡ በተራ ፡ ከሳመች ፡ በኋላ ፡ ትንሹን ፡ ሕፃን ፡ አቅፋ ፡ እያለቀሰች ፡ በድህነቴ ፡ ምክንያት ፡ አባይ ፡ ሆኘ ፡ ልጅ ፡ የለኝም ፡ ብዬ ፡ ዋሽሁ ። ጐሽ ፡ ለልጆችዋ ፡ ስትል ፡ ትወጋለች ። እንደተባለው ፡ እኔም ፡ ለናንተ ፡ ስል ፡ ሕይወቴን ፡ ለማሻሻል ፡ የቅድማያቴንና ፡ ያያቴን ፡ ክብር ፡ ረስቼ ፡ ለገንዘብ ፡ ስል ፡ አባይ ፡ ዋሾ ፡ ሆንኩ ፡ እያለች ፡ ዕንባዋን ፡ ካፈሰሰች ፡ በኋላ ፡ ለልጆችዋና ፡ ለስዋ ፡ ምግብ ፡ ለማሰናዳት ፡ ወደ ፡ ማድቤት ፡ ሔደች ።




ላጋር ፡ የባቡር ፡ መቋሚያ ።

# ምዕራፍ ፡ ፫ ፡

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሰባት ፡ ሰዓት ፡ የተገኘውን ፡ ምግብ ፡ ከእንጨት ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ አቅርባ ፡ እርስዋም፡ ልጆችዋም ፡ ምሳቸውን ፡ ተጋብዘው ፡ እንደዚሁም ፡ ራታቸውን ፡ በልተው ፡ ተኙ ። ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ በማለዳ ፡ ተነሥታ ፡ ከልጆችዋ ፡ ጋር ፡ ቁርስ ፡ አድርጋ ፡ ወደ ፡ እምትወዳት ፡ ጐረቤትዋ ፡ ዘንድ ፡ ሔዳ ፡ ደህና ፡ ልብስ ፡ ተውሳ ፡ መጣች ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከልጆችዋ ፡ ጋር ፡ ምሳዋን ፡ በልታ ፡ ለራታቸው ፡ የሚበቃ ፡ አሰናድታላቸው ፡ ለትልቅዋ ፡ ልጅዋ ፡ አደራሺን ፡ የተስፋዬን ፡ ነገር ፡ ደህና ፡ አድርገሽ ፡ ጠብቂው ፡ ብላ ፡ ሦስቱንም ፡ ልጆችዋን ፡ ስማ ፡ በ፱ ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በኦቶቡስ ፡ ተሳፍራ ፡ ሔደች ።

እስዋም ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ፍል ፡ ውሃ ፡ ሔዳ ፡ ታጥባ ፡ ልብስዋንም ፡ ለውጣ ፡ በቀጠሮዋ ፡ ልክ ፡ በሁለት ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ቤት ፡ ሔደች ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ዘንግቶት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የተቃጠራት ፡ ብዙ ፡ ከአሜሪካንና ፡ ከእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ተምረው ፡ ዲግሪያቸውን ፡ ተቀብለው ፡ ለመጡ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ወጣቶች ፡ ባልንጀሮቹ ፡ የክብር ፡ ግብዣ ፡ ስላደረገ ፡ የውጪም ፡ አገር ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ተጠርተው ፡ ስለነበረ ፡ ወንዶቹ ፡ በፍራክ ፡ ሴቶቹ ፡ በአልማዝና ፡ በወርቅ ፡ አጊጠው ፡ ሲገቡ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ በቀጠሮዋ ፡ መጥታ ፡ ከበራፍ ፡ ቆማ ፡ በመደነቅ ፡ ትመለከት ፡ ነበር ።

ወዲያው ፡ አንድ ፡ አሽከር ፡ ወደርስዋ ፡ መጥቶ ፡ ከዚህ ፡ ምን ፡ ታደርጊያለሽ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃት ።

ፀሐደ ፡ መስፍን ፡ ልጅ ፡ ዓለም ፡ ደስታ ፡ ዛሬ ፡ ማታ ፡ በሁለት ፡ ሰዓት ፡ እንድመጣ ፡ ቀጥሮኝ ፡ ነበር ።

አሽከሩ ፡ ስምዎ ፡ ማነው ፡

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ከኰሮጆዋ ፡ ስምዋ ፡ የተጻፈበትን ፡ ካርት ፡ አውጥታ ፡ ሰጠችው ።

አሽከሩም ፡ ሔዶ ፡ ካርት ፡ ቢዚቱን ፡ ሰጠው ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ያስበበት ፡ ባደረገው ፡ ቀበሮ ፡ ተናዶ ፡ ከበዓሉም ፡ ውስጥ ፡ እንዳትገባ ፡ የማታ ፡ ልብስ ፡ ስለሌላት ፡ ታሳፍረኛለች ፡ ብሎ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተከዞ።

ከቆየ ፡ በኋላ ፡ ከካርታዋ ፡ ጀርባ ፡ ላይ የኔ ፡ ወዳጅ ፡ ይቅር ፡ በይኝ ፡ ዛሬ ፡ ቀጠሮ ፡ ያደረግሁት ፡ ተሳስቼ ፡ ነው ።

ኣሁንም ፡ ይህ ፡ አሽከር ፡ ከሚያሳይሽ ፡ ቤት ፡ ገብተሽ ፡ እንግዶቼን ፡ ሸኝቼ ፡ እስከመጣ ፡ ድረስ ፡ ጠብቂኝ ፡ ብሎ ፡ ጽፎ ፡ ላሽከሩ ፡ ይህንን ፡ ሰጣትና ፡ ከሦስተኛው ፡ ደርብ ፡ ላይ ፡ አውጣና ፡ ላሽከሮች ፡ ከተሰናዳው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ አስገባትና ፡ ትቆይ ፡ አለው ።

አሽከሩም ፡ ካርት ፡ ቪዚቱን ፡ ሰጥቶ ፡ ወዲያው ፡ ይዝዋት ፡ ከሦስተኛው ፡ ደርብ ፡ ወጥተው ፡ ካንድ ፡ ክፍል ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ አልጋና ፡ አንድ ፡ ጠረጴዛ ፡ ሁለት ፡ ወንበር ፡ ካለበት ፡ ክፍል ፡ አስገብትዋት ፡ ሔደ ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ያንኑ ፡ ባልንጀራዋን ፡ የድሆች ፡ ከተማ ፡ የሚባለውን ፡ መጽሐፍ ፡ ከጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ ዘርግታ ፡ መብራትዋን ፡ አብርታ ፡ አባ ፡ ሰው ፡ በከንቱ ፡ የሚባሉ ፡ መነኩሴ ፡ ካብ ፡ ካብትህ ፡ ይመርጋር ፡ የተከራከሩበትን ፡ ስትመለከት ፡ ዳንስ ፡ ተጀምሮ ፡ የሙዚቃ ፡ ድምፅ ፡ ትሰማ ፡ ጀመር ።

ከጥቂት ፡ ሰዓት ፡ በኋላ ፡ ላቨሽ ፡ ጅዋየዝ ፡ የሚባለው ፡ ቫልስ ፡ ሰምታ ፡ በጣም ፡ አዘነች ።

ምክንያቱም ፡ የሞተውን ፡ ባልዋንና ፡ አሁን ፡ ከደስታና ፡ ከኃዘን ፡ መካከል ፡ ሆና ፡ ከባዶ ፡ ቤት ፡ ተዘግቶባት ፡ የሰዎችን ፡ ደስታ ፡ በሩቅ ፡ ሰሚ ፡ ሆና ፡ በመቀመጥዎ ፡ ነው ። ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የዕድል ፡ አበባ ፡ ከገረጣ ፡ በኋላ ፡ ለማሻሻል ፡ ችግር ፡ ነው ። ያው ፡ ክፉ ፡ ዕድሌ ፡ አለቀሽ ፡ ብሎ ፡ ልጆቼን ፡ ከባዶ ፡ ቤት ፡ ጥዬ ፡ የካብታሞችን ፡ ደስታ ፡ ፡ እንዳላይ ፡ እንኳ ፡ ከባዶ ፡ ቤት ፡ ተዘግቶብኛል

፡ አዬ ፡ ጉድ ፡ እንደምን ፡ ያለ ፡ ውርደት ፡ ደረሰብኝ ፡ እያለች ፡ ስታዝን ፡ ከወንበር ፡ ላይ ፡ እንደሆነች ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ የኃዘንና ፡ የተስፋ ፡ መቁረጥ እንቅልፍ ፡ ወሰዳት ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በሕልምዋ ፡ የምትወደው ፡ ልጅዋ ፡ ተስፋዬ ፡ ሌሊት ፡ ከእንቅልፉ ፡ ባኖ ፡ እማማ ፡ እማማ ፡ እማማ ፡ እያለ ፡ በመኝታዋ ፡ ቤት ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ መስኮት ፡ ወጥቶ ፡ ከፎቁ ፡ ላይ ፡ ተወርውሮ ፡ ከመሬት ፡ ሲከሰከስ ፡ አይታ ፡ በድንጋጤ ፡ ባና ፡ ራስዋን ፡ ይዛ ፡ ልጄ ፡ ተስፋዬ ፡ ምን ፡ ሆነህ ፡ ይሆን ፡ ወይኔ ፡ ዕድለ ፡ ቢስዋ ፡ የካብታሞችን ፡ ደስታና ፡ ሁካታ ፡ ለመስማት ፡ ከባዶ ፡ ቤት ፡ ተዘግቶብኝ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንኳ ፡ ተለይቼህ ፡ የማላውቅ ፡ ልጄ ፡ ምን ፡ አደጋ ፡ አግኝቶህ ፡ ይሆን ፡ ብላ ፡ ሰዓትዋን ፡ ብታይ ፡ ከሌሊቱ ፡ ፱ ፡ ሰዓት ፡ ሆንዋል ።

ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የድሆች ፡ ከተማ ፡ የሚባለውን ፡ መጽሐፍ ፡ ከጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ እንደዘረጋችው ፡ ትታ ፡ በደረጃው ፡ እየሮጠች ፡ ወርዳ ፡ በሩን ፡ በኃይል ፡ ከፍታ ፡ ከወጣች ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አቃቂ ፡ በሰቃ ፡ ትሮጥ ፡ ጀመር ።

ቀኑ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ስለነበረ ፡ ብዙ ፡ ዝናም ፡ ይጥል ፡ ነበርና ፡ ያቺ ፡ ዕድለ ፡ ቢስ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ በዚያ ፡ በዝናምና ፡ በሰማዩ ፡ ብልጭታ ፡ እየደነገጠች



ኰሎንኣልፒ ፡

ስስ ፡ ካሎስ ፡ ቀሚስ ፡ እንደለበሰች ፡ በብርድ ፡ እየተንቀጠቀጠች ፡ ስትሮጥ ፡ ስትወድቅ ፡ ስትነሳ ፡ ልጁ ፡ ልጁ ፡ እያለች ፡ ስትጮህ ፡ ያያት ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ መኖር ፡ አያስመኝም ፡ ነበር ።

እንደዚሁም :እየሮጠች ፡ ኮሎናልፒ ፡ አጠገብ ፡ ስትደርስ ፡ አንድ ፡ ካሚዮን ፡ እህል ፡ ጭኖ ፡ ሲመጣ ፡ አግኝታ ፡ እባክህ ፡ አቃቂ ፡ አድርሰኝ ፡ ብላ ፡ እየጮኸች ፡ ከዳር ፡ ሮጣ ፡ መጥታ ፡ ከመካከል ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ወደቀች ።

ነጂው ፡ አላያትም ፡ ነበርና ፡ በላይዋ ፡ ላይ ፡ ሊሔድ ፡ ጥቂት ፡ ሲቀረው ፡ ከፊቱ ፡ አንድ ፡ ነጭ ፡ ነገር ፡ ወድቆ ፡ ስላየ ፡ ፍሬኑን ፡ በኃይል ፡ አቆመና ፡ ከካሚዮኑ ፡ ወርዶ ፡ ከመሬት ፡ ላይ ፡ ቢያነሣት ፡ በዝናብና ፡ በጭቃ ፡ ከራስዋ ፡ እስከ ፡ እግርዋ ፡ የተጨማለቀች ፡ ወጣት ፡ መሆንዋን ፡ ካየ ፡ በኋላ ፡ ይህች ፡ ቅሬ ፡ ሸርሙጣ ፡ የዓለም ፡ ሴት ፡

ከማን ፡ ቤት ፡ ኣድራ ፡ ሰክራ ፡ ነው ፡ ልትናጥ ፡ የነበረ ፡ ብሎ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ በጥፊ ፡ መትቷት ፡ ከመንገዱ ፡ ውጪ ፡ ገፍቶ ፡ ጣላትና ፡ በካሚዮኑ ፡ ወጥቶ ፡ ሔደ ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ በደረሰባት ፡ መከራ ፡ ላይ ፡ ተጨማሪ ፡ ሁለት ፡ ጥፊ ፡ በሾፌሩ ፡ እጅ ፡ ስለተመታች ፡ አዞርዋት ፡ ራስዋን ፡ በጅዋ ፡ ደግፋ ፡ ከቆየች ፡ በኋላ ፡ ተነሥታ ፡ ወደ ፡ አቃቂ ፡ ትሮጥ ፡ ጀመር ። ፲፩ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲሆን ፡ አቃቂ ፡ ወንዝ ፡ ደረሰች ።


እስዋም ፡ ከድልድዩ ፡ ኣጠገብ ፡ ቆማ ፡ ውሀው ፡ ሞልቶ ፡ ፈረሰኛው ፡ ሲዘል ፡ አይታ ፡ ከቤቴ ፡ ገብቼ ፡ የልጄን ፡ የተስፋዬን ፡ ሞት ፡ ከመስማት ፡ ከዚህ ፡ ወንዝ ፡ ላይ ፡ ወድቄ ፡ መሞት ፡ ይሻለኛል ፡ እያለች ፡ ሁለት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ እጅዋን ፡ እንደ ፡ መስቀል ፡ ዘርግታ ፡ አቤቱ ፡ እኔን ፡ ኃጢአተኛ ፡ ባሪያህን ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ ራሴን ፡ በራሴ ፡ ብገድል ፡ ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ መሆኔን ፡ ሳውቅ ፡ ይህንን ፡ ኃጢአት ፡ ለመሥራት ፡ ያስጨከነኝን ፡ አንተ ፡ ልብንና ፡ ኩላሊትን ፡ የምትመረምር ፡ ታውቀዋለህ ፡

እኔ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያየት ፡ የቅድማያቴን ፡ ዕዳ ፡ ከፋይ ፡ ሆኜ ፡ ብዙ ፡ ፈተና ፡ እንደደረሰብኝ ፡ ካንተ ፡ የሚሠወር ፡ አይደለም ።

እኔም ፡ የልጆቼን ፡ ኑሮ ፡ ለማሻሻል ፡ ልጆች ፡ የሉኝም ፡ ብዬ ፡ አንተ ፡ የሰጠኸኝን ፡ በረከት ፡ ካድሁ ።

በቃሌ ፡ ኣሰት ፡ ተናግሬ ፡ የማላውቀውን ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ የካብታም ፡ ልጅ ፡ ለማግባት ፡ አባይ ፡ ዋሾ ፡ በመሆኔ ፡ የቅድማያቶቼንና ፡ ያያቶቼን ፡ ስም ፡ አሳደፍሁ ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሆኖ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ውርደት ፡ የደረሰብኝ ፡ ለተስፋዬ ፡ ለልጄ ፡ ነበር ። እንግዲህ ፡ እሱበእንደዚህ ፡ ያለ ፡ አማት ፡ ከሞተ ፡ እኔ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ለመኖር ፡ አያስፈልገኝም ።



ያቃቂ ፡ ወንዝ ።

አቤቱ ፡ ነፍሴን ፡ አደራ ፡ ብላ ፡ ዘላ ፡ ከባሕሩ ፡ ላይ ፡ ልትወረወር ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያትን ፡ ስትደግም ፡ አንድ ፡ ከጐረቤትዋ ፡ የሚረዳት ፡ ካብታም ፡ ነጋዴ ፡ ተሰማ ፡ ኃዘኔ ፡ የሚባል ፡ የጐጃም ፡ ተወላጅ ፡ በኦቶመቢል ፡ ሆኖ ፡ በፍጥነት ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ ሲመጣ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ እጅዋን ፡ ዘርግታ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ልትወረወር ፡ ስትል ፡ ካጠገብዋ ፡ በኃይል ፡ ኦቶመቢሉን ፡ አቆመ ።

እስዋም ፡ ምን ፡ መጣብኝ ፡ ብሳ ፡ ደንግጣ ፡ ወደሱ ፡ ስትዞር ፡ አይትዋት ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ ታቅፎ ፡ ብድግ ፡ አድርጎ ፡ ከኦቶሞቢል ፡ ውስጥ ፡ አስቀመጣት ።

# ምዕራፍ ፡ ፮

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ድልድዩን ፡ ተሻግሮ ፡ ከመንገድ ፡ ወጣ ፡ ብሎ ፡ ቁሞ ፡ ልጄ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ምን ፡ ነገር ፡ አግኝቶሽ ፡ ነው ፡ እንደዚህ ፡ በዝናብ ፡ እስከ ፡ አጥንትሽ ፡ እርሰሽ ፡ እንደ ፡ አበደች ፡ ሴት ፡ የሆንሽው ፡ ደህና ፡ ልጅ ፡ አልነበርሽምን ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ደህና ፡ ነበርሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ በመሆኔ ፡ እንደዚህ ፡ ትዋረድሁ ። እግዚአብሔር ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ አይስጥዎ ፡ እያለች ፡ ታለቅስ ፡ ጀመር ።

አቶ ፡ ተሰማ ፡ ኃዘኔም ፡ እንደዚህ ፡ ሴት ፡ መነሆንሽን ፡ የሚያስጠላ ፡ ምን ፡ ነገር ፡ አገኘሽ ፡

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ እርስዎም ፡ እንደሚያውቁት ሦስት ፡ የሙት ፡ ልጆቼን ፡ ይዤ ፡ ድህነቴን ፡ ለምጄ ፡ ከድሀ ፡ ጐጆዬ ፡ ስኖር ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ፲፪ ፡ የካቲት ፡ አደባባይ ፡ አጠገብ ፡ ካለጽታ ፡ ከሕንፃ ፡ አታክልት ፡ ውስጥ ፡ ተቀም ጩጩ ፡ መጽሐፍ ፡ ስመለከት ፡ አንድ ፡ ወጣት ፡ የካብታም ፡ ልጅ ፡ አጠገቤ ፡ ከድንጋይ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ስንጫወት ፡ የመውደድ ፡ አኳኋን ፡ አሳየኝ ።

እኔም ፡ የልጅና ፡ የሴት ፡ ነገር ፡ ሆኖብኝ ፡ በመልኩና ፡ በትምህርቱ ፡ ተስቤ ፡ ይልቁንም ፡ ጐሽ ፡ ለልጆችዋ ፡ ስትል ፡ ትወጋለች ፡ እንደተባለው ፡ የልጆቼን ፡ ሕይወት ፡ ለማሻሻል ፡ ስል ፡ ቶሎ ፡ ብዬ ፡ ፍቅሬን ፡ ገለጥኩለት ።

ይልቁንም ፡ በጣም ፡ የሚያሳዝነኝ ፡ እንዳይተወኝ ፡ በማለት ፡ ልጆች ፡ የሉኝም ፡ ብዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰጠኝን ፡ ልጆች ፡ ካድሁ ።

ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቆጥቶኝ ፡ የምወደው ፡ ልጄ ፡ ተስፋዬ ፡ ሞተብኝ ።

አቶ ፡ ተሰማ ፡ ኃዘኔ ፡ በጣም ፡ ደንግጦ ፡ መቼ ፡ ነው ፡ የሞተው ፡ ማነው ፡ የነገረሽ ፡

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ጌታዬ ፡ ቅድም ፡ እንደነገርኩዎ ፡ ያ ፡ ላግባሽ ፡ ያለኝ ፡ ወዳጄ ፡ ትናንት ፡ ማታ ፡ ከናቱ ፡ ጋር ፡ ለማስታዋወቅና ፡ የጋብቻችንን ፡ ነገር ፡ ለመጨረስ ፡ በሁለት ፡ ሰዓት ፡ ማታ ፡ ስለጠራኝ ፡ በቀጠሮዬ ፡ ብሔድ ፡ ትልቅ ፡ በዓል ፡ ሆኖ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ወጣቶች ፡ የራት ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ ሴቶችም ፡ በአልማዝና ፡ በወርቅ ፡ አጊጠው ፡ ሲገቡ ፡ አይቼ ፡ መምጣቴን ፡ ካርቴን ፡ ብልክለት ፡ ካሽከሮች ፡ ማደሪያ ፡ ከሦስተኛው ፡ ደርብ ፡ ላይ ፡ ወጥቼ ፡ እንድጠብቀው ፡ ላከብኝ ፡ እኔም ፡ ላስጨርሰው ፡ ብዬ ፡ ከሌሊቱ ፡ እስከ ፡ ስምንት ፡ ሰዓት ፡ ጠበቅሁት።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የኃዘንና ፡ የብስጭት ፡ የጠለቀ ፡ እንቅልፍ ፡ ጠረጴዛውን ፡ ተደግፌ ፡ ተኝቼ ፡ ልጄ ፡ ተስፋዬ ፡ እማማ ፡ እማማ ፡ እያለ ፡ ከመኝታዬ ፡ ቤት ፡ ፎቅ ፡ ወድቆ ፡ ከመሬት ፡ ላይ ፡ ሲከሰከስ ፡ እኔው ፡ ራሴ ፡ አየሁት ፡ አለችው ።

አቶ ፡ ተሰማ ፡ ኃዘኔ ፡ በጣም ፡ አዝኖ ፡ በውኔት ፡ በዚያ ፡ በካብታም ፡ ልጅ ፡ ፍቅር ፡ ምክያንት ፡ ራስሽ ፡ ዞሮ ፡ አብደሻል ፡ ሕልሙን ፡ እንደ ፡ ውን ፡ አድርገሽ ፡ እንደዚህ ፡ አድርጎ ፡ ማልቀስ ፡ ይገባልን ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ጌታዬ ፡ የልጄ ፡ ሞት ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ። እርስዎም ፡ በኦቶመቢል ፡ እየሮጡ ፡ የመጡት ፡ ይህንን ፡ ጉዳቴን ፡ ሰምተው ፡ ነው ። እባክዎ ፡ በልጅ ፡ አምላክ ፡ ወስደው ፡ ሳይቀብሩት ፡ ስሜው ፡ እንድሰናበተው ፡ ይዘውኝ ፡ ቶሎ ፡ ይሒዱ ፡ ብላከእግሩ ፡ ላይ ፡ ወድቃ ፡ ትለምነው ፡ ጀመር ።

አቶ ፡ ተሰማ ፡ ኃዘኔ ፡ እያለቀሰ ፡ ከእግሩ ፡ ላይ ፡ አንስቶ ፡ በኦቶመበል ፡ ይዋት ፡ ሔደ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከቀኑ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ይሆን ፡ ነበር ።

እንደደረሰች ፡ ኦቶመቢሉን ፡ በኃይል ፡ ከፍታ ፡ ወደ ፡ ቤትዋ ፡ ልትገባ ፡ ስትል ፡ ሁለቱ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ መምጣትዋን ፡ ያጠባበቁ ፡ ኖሮ ፡ የናፍቆትና ፡ የደስታ ፡ ዕንባ ፡ እያፈሰሱ ፡ ከላይዋ ፡ ላይ ፡ ተጠመጠሙ ። ትንሽዋን ፡ ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ ሞተ ፡ ወይ ፡ ብላ ፡ ብትጠይቃት ፡ አዎን ፡ እማማ ፡ አለቻት ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ኡ ፡ ኡ ፡ ኡ ፡ እያለች ፡ ራስዋን ፡ ከመሬት ፡ እየከሰከሰች ፡ ስትጮህ ፡ ጐረቤት ፡ ሁሉ ፡ ሰምቶ ፡ ተሰበሰበ ።

ሁሉም ፡ ኣቶ ፡ ተሰማ ፡ ኃዘኔን ፡ ምን ፡ ሆነች ፡ እያሉ ፡ ይጠይቁት ፡ ጀመር ።

እሱም ፡ ተስፋዬ ፡ የሚባለው ፡ ልጅዋ ፡ ሞተ ፡ ብለው ፡ ስለነገርዋት ፡ ነው ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ ማነው ፡ የነገራት ፡ ብለው ፡ ቢጠይቁት ፡ ይህች ፡ ህፃን ፡ ልጅ ፡ ናት ፡ አላቸው ። ጐረቤቶቹም ፡ ሕፃንዋን ፡ ልጅ ፡ ጠርተው ፡ አንቺ ፡ ልጅ ፡ ወንድምሽ ፡ መቼ ፡ ነው ፡ የሞተው ፡ ብለው ፡ ቢጠይቅዋት ፡ ትላንትና ፡ ማታ ፡ ተኝቶ ፡ አሁንም ፡ ከዚያው ፡ እንደተኛ ፡ ነው ። አለቻቸው ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ፎቁ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ የማይዝ ፡ ስለሆነ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ወጥተው ፡ ቢያዩ ፡ ተስፋዬ ፡ ከንቅልፉ ፡ ነቅቶ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ዓይኑን ፡ ሲጠራርግ ፡ አገኙትና ፡ ይዘውት ፡ ወረዱ ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ባየችው ፡ ጊዜ ፡ እውነት ፡ አልመሰል ፡ ብልዋት ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ አውጥታ ፡ እየተመለከተች ፡ ትስመው ፡ ጀመር ።

ጐረቤቶችዋም ፡ ሁሉ ፡ የመረረ ፡ ኃዘንዋን ፡ ስላዩ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ደስታ ፡ አደረጉ ።

ይልቁንም ፡ ኣቶ ፡ ተሰማ ፡ ኃዘኔ ፡ ደም ፡ ብሎ ፡ በልጅዋ ፡ ሞት ፡ ተስፋ ፡ ቆርጣ ፡ ዘላ ፡ ካቃቂ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ልትወድቅ ፡ ስትል ፡ ስለደረሰባትና ፡ ከጐረቤቶችዋም ፡ ጋር ፡ ተጨናቂ ፡ ሆኖ ፡ ስለነበረ ፡ የበለጠ ፡ ደስ ፡ አለው ።




የዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ሆስፒታል

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ እስከ ፡ አቃቂ ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ የዝናብ ፡ መዓት ፡ ሲወርድባት ፡ ስለነበረ ፡ ከራስዋ ፡ እስከ ፡ እግርዋ ፡ ድረስ ፡ ርሳ ፡ ትንቀጠቀጥ ፡ ነበር ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከጐረቤቶችዋ ፡ አንዲቱ ፡ በጣም ፡ የምትወዳትና ፡ የምታስብላት ፡ ወሰንየለሽ ፡ ተገኝ ፡ የምትባል ፡ ሴት ፡ የራስዋን ፡ የውስጥ ፡ ልብስ ፡ አምጥታ ፡ ያንን ፡ የተዋሰችውን ፡ ካሎስ ፡ አውልቃ ፡ የስዋን ፡ የውስጥ ፡ ልብስ ፡ አልብሳ ፡ ካልጋ ፡ ላይ ፡ አስተኛቻት ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ በጣም ፡ በብርድ ፡ ስለተነካች ፡ ስል ፡ ጀመር ።

ይልቁንም ፡ ውጋት ፡ በግራ ፡ ጐንዋ ፡ ቀስፎ ፡ ስለያዛት ፡ ቡናም ፡ ቻይም ፡ ለመቅመስ ፡ እየለበቃት ፡ የማትውጥ ፡ ሆነች ።

ስለዚህ ፡ አቶ ፡ ተሰማ ፡ ኃዘኔና ፡ ወይዘሮ ፡ ወሰን ፡ የለሽ ፡ ተገኝ ፡ እልፍ ፡ ብለው ፡ ይህች ፡ ልጅ ፡ በጣም ፡ በብርድ ፡ ምክንያት ፡ ታማለች ፡ ስለዚህ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ወስደን ፡ ከዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ሆስፒታል ፡ እናስተኛት ። ዋጋውንም ፡ ሁለታችን ፡ ተካፍለን ፡ እንከፍላለን ። ተባብለው ፡ ወደ ፡ ሆስፒታል ፡ ወስደው ፡ አስተኝዋት ።

ልጆቹንም ፡ ሁለቱን ፡ አቶ ፡ ተሰማ ፡ ኃዘኔ ፡ አንዲቱን ፡ ወይዘሮ ፡ ወሰን ፡ የለሽ ፡ ወስደው ፡ ከልጆቻቸው ፡ ጋራ ፡ ቀላቀልዋቸው ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ደዌዋ ፡ እየጠናበት ፡ ሔደ ፡ ሐኪሞቹም ፡ ብል ፡ ፐሊሞኒ ፡ ስለሆነ ፡ ሳምባዋ ፡ ሁሉ ፡ በመያዙ ፡ ምንም ፡ ተስፋ ፡ የለም ፡ ብለው ፡ ተመልሳ ፡ ከቤትዋ ፡ እንድትተኛ ፡ ስላስታወቁ ፡ አቶ ፡ ተሰማ ፡ ኃዘኔ ፡ በኦቶመስል ፡ ከቤትዋ ፡ ወስዶ ፡ አስተኛት ። ልጆችዋንም ፡ እያመጡ ፡ ሰጡዋት ።

ያች ፡ ችግረኛ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ያያት ፡ የቅድማያትዋን ፡ ዕዳ ፡ ከፋይ ፡ ሆና ፡ ካልጋዋ ፡ ላይ ፡ ተጋድማ ፡ ዓጽም ፡ መስላ ፡ ልጆችዋ ፡ ዙሪያዋን ፡ ከበዋት ፡ እንደዚህ ፡ እያለች ፡ የለቅሶ ፡ ዜማ ፡ ታንጐራጕር ፡ ነበር።

> አባቴ ፡ በገፁ ፡ አያቴ ፡ በነዱ ።
> እኔን ፡ ዕዳ ፡ ከፋይ ፡ አድርገውኝ ፡ ሔዱ ።
> ገዝተው ፡ እንዲያው ፡ አይሔዱም ፤
> ድላል ፡ አለ ፡ አሉ ፡ በምድርም ።

እያለች ፡ ወይ ፡ ልጆች ፡ ለምን ፡ ተፈጠራችሁ ፡ ትላቸው ፡ ነበር ።

# ምዕራፍ ፡ ፳ ፡

እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ታሪክ ፡ እንመለስ ።

ልጅ ፡ ዓስሙ ፡ ደስታ ፡ በበዓሉ ፡ ምክንያት ፡ ደክሞት ፡ ተኝቶ ፡ ረስትዋት ፡ ጠዋት ፡ በሁለት ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ነቅቶ ፡ ከዚያው ፡ ካሽከሮች ፡ ቤት ፡ ተኝታ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ ቢወጣ ፡ እስዋ ፡ ሔዳ ፡ የድሆች ፡ ከተማ ፡ የሚባለውን ፡ መጽሐፍ ፡ ተዘርግቶ ፡ አገኘው

እሱም ፡ ከዚያው ፡ ከወንበር ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ መስመር ፡ ያነብ ፡ ነበር ። ቃሉ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ሰው ፡ ሆይ ፡ ትላንት ፡ ስሙ ፡ ጥሩ ፡ ካብታም ፡ የነበርክ ፡ ዛሬ ፡ ማነህ ፡ የተዋረድክ ፡ ድሀ ፡ አፈር ፡ ትቢያ ፡ አይደለህምን ፡ የሚለውን ፡ ካነበበ ፡ በኋላ ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ ቢመለከት ፡ ዘመድ ፡ ወዳድህ ፡ ሸኝተውህ ፡ ተመለሱ ፡ ከሁሉ ፡ ኣብልጠህ ፡ የምትወደው ፡ ወዳጅህ ፡ ግን ፡ ከመቃብር ፡ ድረስ ፡ ስንኳን ፡ አልሸኘህም ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ሲጨርስ ፡ ለዚህ ፡ ለሚያልፍ ፡ ደስታ ፡ ድሀ ፡ ነኝ ፡ በማለት ፡ ወዳጄን ፡ ፀሐይ ፡ መስፍንን ፡ አሳዘንኳት ።

እንግዲህ ፡ ሔጄ ፡ ልፈልጋትና ፡ ይቅርታ ፡ ልለምን ፡ እያለ ፡ ሲያስብ ፡ አንድ ፡ ደብዳቤ ፡ ካውራ ፡ ጎዳና ፡ ባለ ፡ ሥልጣን ፡ ዲሬክተር ፡ ደረሰው ። ካንቦልኩም ፡ ላይ ፡ በጣም ፡ የሚያስቸኩል ፡ ስለሚል ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ ቢከፍተው ፡ አሁን ፡ በፍጥነት ፡ መጥተህ ፡ ወዳስመራ ፡ እንድትሔድ ፡ አይሮፕላኑም ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ይጠብቅሃል ፡ የጉዳዩን ፡ ማስታወሻ ፡ ከዚያው ፡ ካይሮፕላኑ ፡ ድረስ ፡ ተልኮልሃል ፡ የሚል ፡ ነው።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ ቁርሱን ፡ በልቶ ፡ ባንድ ፡ ትንሽ ፡ ሳጥን ፡ ልብሶቹን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ አይሮፕላን ፡ ሜዳ ፡ ሔዶ ፡ ተሳፈረ ።



ያይሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ተኩል ፡ አሥመራ ፡ ቆይቶ ፡ ኣዲስ ፡ አበባ ፡ ተመለሰ ።

ወዲያው ፡ እንደደረሰ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍንን ፡ ይፈልግ ፡ ጀመር ።

ምናልባት ፡ ፲፪ ፡ የካቲት ፡ አደባባይ ፡ አጠገብ ፡ ካለው ፡ የሕዝብ ፡ አታክልት ፡ ውስጥ ፡ ትመጣ ፡ ይሆን ፡ በማለት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቢሔድ ፡ ሳያገኛት ፡ ቀረ ።

ሰዎችንም ፡ ቢጠይቅ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ የምትባል ፡ ልጃገረድ ፡ አናውቅም ፡ አሉት ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ካቃቂ ፡ ዓሣ ፡ ይዞ ፡ ለመሸጥ ፡ ወደ ፡ ኣዲስ ፡ አበባ ፡ መጥቶ ፡ በየመንገዱ ፡ ዓሣውን ፡ ለመሸጥ ፡ ሲዞር ፡ ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ በካዲላክ ፡ ኦቶመቢል ፡ ውስጥ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ቤንዚን ፡ ሲያስሞላ ፡ ዓሣ ፡ ወጋሪውን ፡ ጠርቶ ፡ ይህን ፡ ዓሣ ፡ ከወዴት ፡ ዓመጣኸው ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ።

እሱም ፡ ካቃቂ ፡ ወንዝ ፡ ውስጥ ፡ በመንጠቆ ፡ ያዝኳቸው ። ያቃቂ ፡ ዓሣ ፡ በጣም ፡ ጣፋጭ ፡ ስለሆነ ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ይገዛኛል ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ በዚህ ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ታውቃለህን ።

ዓሣ ፡ ወጋሪው ፡ የሚበልጠውን ፡ ሰው ፡ አውቀዋለሁ ። ምክንያቱም ፡ ዘወትር ፡ ትኩስ ፡ ዓሣ ፡ ይዤ ፡ ስለማመጣ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ከቤታቸው ፡ ድረስ ፡ እንዳመጣላቸው ፡ ደንበኛ ፡ አድርገውኛል ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ በመንገድ ፡ እየዞርሁ ፡ የምሸጠው ፡ ከነሱ ፡ የተረፈውን ፡ ነው ።

ልጅ ፡ ዓስሙ ፡ ደስታ ፡ እንግዲያውስ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ልጠይቅህ ፡

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ የምትባለውን ፡ ወጣት ፡ ታውቃለህን ፡ ቤትዋን ፡ ብታሳየኝ ፡ ደህና ጉርሻ ፡ አጕርስህ ፡ ነበር ።

ዓሣ ፡ ወጋሪው ፡ የምትኖረው ፡ ወዴት ፡ ነው

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

ዓሣ ፡ ወጋሪው ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ የምትባል ፡ ልጃገረድ ፡ አላውቅም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እርስዎ ፡ ያውቁዋት ፡ አይመስለኝም ፡ እንጂ ፡ አንዲት ፡ ደሀ ፡ ሴት ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ የምትባል ፡ ሦስት ፡ ልጆች ፡ ያልዋት ፡ ባልዋ ፡ የሞተባት ፡ አቃቂ ፡ አለች ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ መልኳ ፡ ምን ፡ ይመስላል ፡ ቀይ ፡ ናት ፡ ጥቁር ፡

ዓሣ ፡ ወጋሪው ፡ ድሀ ፡ ከመሆንዋ ፡ በስተቀር ፡ እስዋን ፡ የሚመስል ፡ ሴት ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ አይመስለኝም ፡ አበባ ፡ የመሰለች ፡ ቀይ ፡ ናት ። ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ አንድ ፡ ሶስት ፡ ወር ይሆናታል ። አንድ ፡ ካብታም ፡ ወዳጅዋ ፡ ኣሳዝንዋት ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ ኣቃቂ ፡ በዝናብ ፡ በውድቅት ፡ ጨለማ ፡ ስትሮጥ ፡ መጥታ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ጽኑ ፡ ደዌ ፡ ታማለች ፡ ያለ ፡ ጓደኛዋ ፡ ጓደኛ ፡ ይዛ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ በሽታ ፡ ወደቀባት ፡ እያሉ ፡ ጐረቤቶችዋ ፡ ሁሉ ፡ ያዝኑላታል ።

እኔም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ዓሣ ፡ እየያዝሁ ፡ እሰጣታለሁ ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ አጭር ፡ ነች ፡ ረዥም?

ዓሣ ፡ ወጋሪው ፡ ረዘም ፡ ያለች ፡ ሎጋ ፡ ወገብዋ ፡ የንብ ፡ አውራ ፡ የሚመስል ፡ ሾጤ ፡ ልጅ ፡ ናት ። ጌታዬ ፡ በአቃቂ ፡ ከተማ ፡ ቆንጆ ፡ ልጅ ፡ የተወለደች ፡ እንደሆን ፡ ፀሐይ ፡ መስፍንን ፡ ትመስላለች ፡ ይባላል

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ አገርዋ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ይባላል ።

ዓሣ ፡ ወጋሪው ፡ ኣገርዋ ፡ እንደሰማሁት ፡ ሸዋ ፡ ነው ፡ ይባላል ። በአቃቂ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚወራው ፡ ዱሮ ፡ ከመቶ ፡ አምሳ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ኣያቶችዋ ፡ መሳፍንቶች ፡ ናቸው ። በማለት ፡ የከተማው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ጊዜ ፡ የጣላት ፡ የጨዋ ፡ ልጅ ፡ ናት ፡ እያለ ፡ ያዝንላታል ። ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ በውነትም ፡ የጨዋ ፡ ልጅነትዋ ፡ በትሕትናዋ ፡ ይታወቃል ። ለከተማው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንዳሸከር ፡ ዋና ፡ ታዛዥ ፡ ናት።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ እባክህ ፡ ይህቺን ፡ ሴት ፡ ላያት ፡ እወዳለሁና ፡ ቤትዋን ፡ አሳየኝ ።

ዓሣ ፡ ወጋሪው ፡ ይህንን ፡ የተረፈውን ፡ ዓሣ ፡ ለማን ፡ ትቼ ፡ እሔዳለሁ ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ሁሉንም ፡ እኔ ፡ እገዛሃለሁ ። ዋጋውን ፡ ንገረኝ ።

ዓሣ ፡ ወጋሪው ፡ ዋጋው ፡ ስምንት ፡ ብር ፡ ነበር ፡ ስለርሰዎ ፡ ባምስት ፡ ብር ፡ እሸጥልዎታለሁ ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ስምንቱን ፡ ብር ፡ ሰጥቶ ፡ ሁለት ፡ ብር ፡ ጉርሻ ፡ ጨምሮ ፡ ሰጠውና ፡ ዓሣዎቹን ፡ ከኦቶመቢሉ ፡ ኋላ ፡ ካለው ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ አግብቶ ፡ ቆለፈበት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ኦቶሙቢሉን ፡ እየነዳ ፡ ዓሣ ፡ ወጋሪውን ፡ ከጐኑ ፡ አስቀምጦ ፡ ሾፌሩን ፡ ከኋላው ፡ አስከትሎ ፡ ኦቶመቢሉን ፡ እየነዳ ፡ ከሃሣቡ ፡ ጋር ፡ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ ይጫወት ፡ ነበር ። ይህች ፡ ሴት ፡ ምን ፡ ሴት ፡ ትሆን ፡ የኔ ፡ ወዳጅነች ፡ እንዳልል ፡ ልጆች ፡ አሉዋት ፡ ቤትዋም ፡ አቃቂ ፡ ነው ። የመልኳና ፡ የደም ፡ ግባትዋ ፡ አኳኋን ፡ እንደ ፡ ነገረኝ ፡ ምልክት ፡ እስዋ ፡ ትመስለኛለች ፡ እያለ ፡ ሲያመዛዝን ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ካሽከር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ሳለች ፡ ከጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ተዘርግቶ ፡ ከነበረው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ሰው ፡ ሆይ ፡ ትላንትና ፡ ስመ ፡ ጥሩ ካብታም ፡ የነበርከ ፡ ዛሬ ፡ ማነህ ፡ የተዋረድህ ፡ ድህ ፡ አፈር ፡ ትቢያ ፡ አይደለህምን ፡ ያለውን ፡ እያሰበ ፡ በሞት ፡ በሚለወጥ ፡ ካብቴ ፡ ኮርቼ ፡ ቀጠሮዬን ፡ አፍርሼ ፡ ከባዶ ፡ ቤት ፡ የዘጋሁባት ፡ ወዳጄ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ትሆን ፡ ወይስ ፡ ሌላ ፡ ሴት ፡ ትሆን ፡ እያለ ፡ ሲያስብ ፡ አቃቂ ፡ ደረሰ ።

ከተማውን ፡ ወጣ ፡ ሲል ፡ ዓሣ ፡ ወጋሪው ፡ ጌታዬ ፡ ከዚህ ፡ ነው ፡ ይቁሙ ፡ ብሎ ፡ አቆመና ፡ ሁለቱም ፡ ወርደው ፡ ከቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ገቡ።



አቃቂ ፡ የፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ቤት

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ በሩን ፡ የሚዘጋና የሚከፍት ፡ አሽከር ፡ ስለሌላት ፡ በሩ ፡ ፍክት ፡ ሆኖ ፡ ዶሮች ፡ ይገቡ ፡ ይወጡ ፡ ነበር ።

ሁለቱም ፡ ከቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ቢመለከቱ ፡ ከዶሮች ፡ በስተቀር ፡ ምንም ፡ ሰው።

ሶስቱም ፡ ልጆችዋ ፡ ከፎቅ ፡ ከናታቸው ፡ ጋር ፡ ስለተኙ ፡ ወና ፡ ቤት ፡ መስሎ ፡ ያስደነግጥ ፡ ነበር

ቤቱን ፡ ሁሉ ፡ ቀና ፡ ብለው ፡ ሲመለከቱት ፡ የሸረሪት ፡ ድር ፡ አድርቶበት ፡ ዕቃው ፡ ሁሉ ፡ በያለበት ፡ ተዝረክርኮ ፡ መሬቱም ፡ አልተጠረገም ፡ ነበር ።

# ምዕራፍ ፡ ፲ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዓሣ ፡ ወጋሪው ፡ ጌታዬ ፡ ምናልባት ፡ ሞታ ፡ ለመቃብር ፡ ወስደዋት ፡ እንደሆነ ፡ ጐረቤቶችዋን ፡ እንጠይቅ ፡ ብሎት ፡ ወጡ ።

ወዲያው ፡ በሩን ፡ ሲወጡ ፡ አንዲት ፡ የጐረቤትዋ ፡ ሴት ፡ ከቤትዋ ፡ ወጥታ ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ ከዚህ ፡ ምን ፡ ትፈልጋላችሁ ፡ ብላ ፡ ጠየቀቻቸው ።

እነሱም ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ የምትባለውን ፡ ለመጠየቅ ፡ ነበር ፡ የመጣነው ፡ ከቤትዋ ፡ ብንገባ ፡ ከዶሮዎች ፡ በስተቀር ፡ ምንም ፡ ሰው ፡ ስላላጋኘን ፡ ከጐረቤት ፡ ለመጠየቅ ፡ ወጣን ።

ሴትዮዋም ፡ ኑ ፡ እኔ ፡ አገናኛችኋለሁ ። እስዋ ፡ ግን ፡ በጠና ፡ ታማለች ፡ ብላ ፡ መልሳ ፡ ከቤት ፡ አስገብታ ፡ ጌቶቼ ፡ ከዚህ ፡ ከብርጩማ ፡ ላይ ፡ ተቀመጡ ፡ እኔ ፡ ከፎቅ ፡ ላይ ፡ ወጥቼ ፡ እነግራታለሁ ብላ ፡ አስቀመጠቻቸውና ፡ ስማቸውን ፡ ጠየቀቻቸው ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ በሽተኛዋ ፡ ጽሕፈት ፡ ታውቃለችን ፡

ሴትዮዋ ፡ አወን ፡ ስንኳን ፡ ያገርዋንና ፡ የውጪም ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ ትነጋገራለች ፡ ትጽፍማለች ፡

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ በጣም ፡ ደንግጦ ፡ ካርቱን ፡ አውጥቶ ፡ ሰጣትና ፡ ወጥታ ፡ ለፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ሰጠቻት ። እስዋም ፡ ካልጋዋ ፡ ላይ ፡ እንደተጋደመች ፡ አንብባ ፡ ብድግ ፡ ብላ ፡ ታለቅስ ፡ ጀመር ።

ወዲያው ፡ እኅቴ ፡ ወይዘሮ ፡ ልክም ፡ የለሽ ፡ እባክሽ ፡ አዲሱን ፡ ቀሚሴን ፡ አውጪና ፡ ስጪኝ ፡ ብላ ፡ አዲስ ፡ ቀሚስ ፡ ለብሳ ፡ ወገብዋን ፡ ታጥቃ ፡ ሹራብና ፡ ጫማዋን ፡ አድርጋ ፡ ከወንበር ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ብላ ፡ ጠጉርዋን ፡ ኣበጥራ ፡ ዓይንዋን ፡ ተኩላ ፡ የከሳ ፡ ፊትዋን ፡ በፑድር ፡ ሞልታ ፡ እኅቴ ፡ እባክሽ ፡ በሽተኛ ፡ እመስሳለሁን ፡ አለቻት ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጐረቤትዋ ፡ ዕንባዋ ፡ ባይንዋ ፡ ሞልቶ ፡ እንዳታለቅስ ፡ እየታገለች ፡ ምንም ፡ የታመምሽ ፡ አትመስይም ፡ እያለች ፡ ታጽናናት ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሽቶ ፡ ተቀብታ ፡ ከግድግዳው ፡ ላይ ፡ ከተሰቀለው ፡ መስተዋት ፡ አጠገብ ፡ ሔዳ ፡ ዝወር ፡ ዘወር ፡ እያለች ፡ አምሮባት ፡ እንደሆን ፡ ትመለከት ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልጆችዋን ፡ ወደ ፡ ታች ፡ እንዳትወርዱ ፡ ልጆች ፡ የሚበላ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ አውሬ ፡ ገብትዋልና ፡ እኛ ፡ ሁለታችን ፡ ወርደን ፡ ካባረርነው ፡ ወዲያ ፡ እንጠራችኋለን ፡ በሩን ፡ ዝጉና ፡ ተቀመጡ ፡ ብላ ፡ ነገረቻቸው ።

ልጆቹም ፡ እሺ ፡ እማማ ፡ አንመጣም ፡ በሩን ፡ ዘግተን ፡ እንቀመጣለን ፡ አልዋት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ መታመምዋ ፡ እንዳይታወቅባት ፡ እንደደህና ፡ ሴት ፡ አካሔድዋን ፡ ለማሳመር ፡ ብትሞክር ፡ ሰውነትዋ ፡ በመድከሙ ፡ እየተንገደገደች ፡ ልትወድቅ ፡ ስለሆነ ፡ የወዳጅዋን ፡ እጅ ፡ ይዛ ፡ ወረደች ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ከብርጩማ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ሲመለከት ፡ አንዲት ፡ ምትሃት ፡ የመጣች ፡ መስሎት ፡ ደነገጠ ።

ወዲያው ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ አጠገቡ ፡ ቆማ ፡ እኔ ፡ ወዳጅህ ፡ ነኝ ፡ ስትለው ፡ እንባው ፡ እንደጐርፍ ፡ እየፈሰሰ ፡ ምን ፡ አገኘሽ ፡ የኔ ፡ ወዳጅ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃት ።

ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ በመግደርደር ፡ አኳኋን ታምሜ ፡ ነበር ዛሬ ፡ ደህና ፡ ሆኘልሃለሁ ፡ እያለች ፡ ያለመታመም ፡ መልክ ፡ ስታሳየው ፡ እሱም ፡ በመክሳትዋና ፡ ይልቁንም ፡ በመግደርደር ፡ ደህና ፡ ነኝ ፡ በማለት ፡ ከጽኑ ፡ በሽታዋ ፡ ጋር ፡ ስትታገል ፡ በማየቱ ፡ ራስዋ ፡ የዞረ ፡ መስሎት ፡ በፍርሃት ፡ ይመነለከታት ፡ ነበር ።

ፀሐይ ፡ መስፍንም ፡ እንዳይታወቅባት ፡ እየሳቀች ፡ አይዞህ ፡ ደህና ፡ ነኝ ፡ የኔ ፡ ወዳጅ ፡ የጋብቻችንስ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መቼ ፡ ነው ፡

የሚፈጸም ፡ እኔም ፡ ከብሬን ፡ ጠብቄ ፡ ቆይቼሃለሁ ። ልጆችም ፡ የሉኝ ፡ ከባዶ ፡ ቤት ፡ ብቻዬን ፡ በመሆኔ ፡ እወቀው ፡ እያለች ፡ ስትነግረው ፡ ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ እንደ ፡ ቅዠት ፡ ስለመሰለው ፡ ደንግጦ ፡ ዕንባው ፡ እንደ ፡ ጐርፍ ፡ ይፈስ ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልጆችዋ ፡ ከፎቁ ፡ ላይ ፡ በሩን ፡ ከፍተው ፡ እማማ ፡ እማማ ፡ እያሉ ፡ በደረጃው ፡ ላይ ፡ እየሮጡ ፡ ወረዱ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ በድንጋጤና ፡ በእፍረት ፡ ወዳጅዋን ፡ ትኩር ፡ ብላ ፡ እያየች ፡ እስካሁን ፡ ያታለልኩህ ፡ እብለቴ ፡ ሁሉ ፡ ተገለጠ ። አተን ፡ ለማግባት ፡ ብዬ ፡ የካድኋቸው ፡ ልጆቼ ፡ እኚሁልህ ፡ አደራህን ፡ ብላ ፡ በድንጋጤ ፡ ልብዋ ፡ ስለተመታ ፡ ከመሬት ፡ ላይ ፡ ወድቃ ፡ ሽቅብ ፡ ሽቅብ ፡ ትተነፍስ ፡ ጀመር ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ ደንግጠው ፡ ቆመው ፡ ሲመለከቱ ፡ ዓሣ ፡ ወጋሪውና ፡ ጐረቤትዋ ፡ ወይዘሮ ፡ ልክም ፡ የለሽ ፡ ከመሬት ፡ ላይ ፡ አንሥተው ፡ ካንዲት ፡ ድንክ ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ አጋደምዋትና ፡ የጣር ፡ ትንፋሽ ፡ ትተነፍስ ፡ ጀመር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ እያለቀሰ ፡ ካጠገብዋ ፡ ቀርቦ ፡ ወዳጄ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ደዌ ፡ የወደቀብሽ ፡ አላት ። እስዋም ፡ የወቀሳው ፡ ቀን ፡ አልቋል ፡ ይልቁንስ ፡ ልጆቼን ፡ አደራ ፡ ብላ ፡ እንደ ፡ ወፍ ፡ ድምፅ ፡ አሰምታ ፡ እንግዲህ ፡ አረፍሁ ፡ ብላ ፡ አንገትዋን ፡ አዘነበለችና ፡ አረፈች ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጐረቤቶችዋ ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፡ ያለቅሱ ፡ ጀመር።

ወዲያው ፡ የበሰቃ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ካህናቶች ፡ ተጠርተው ፡ መጥተው ፡ ፍታት ፡ ጀመሩ ። ፍታቱንም ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጉዞ ፡ ጀመሩ ።



የበሰቃ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ በእግሩ ፡ ሬሳውን ፡ ተከትሎ ፡ ያለቅስ ፡ ነበር።

ከቀብሩ ፡ በኋላ ፡ ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታና ፡ ጐረቤቶቹዋም ፡ ሁሉ ፡ ተመልሰው ፡ ከዚያች ፡ ከድሀ ፡ ጐጆዋ ፡ ገብተው ፡ ከየቤታቸው ፡ ቆሎና ፡ ንፍሮ ፡ አምጥተው ፡ ቀባሪዎቹን ፡ አስተናገዱ ።

ከእኩለ ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ በ፲ ፡ ሰዓት ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ የልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ እናትና ፡ የጥቅም ፡ ጓደኞቹ ፡ ያባቱ ፡ አክሲዮን ፡ ያለበት ፡ ማኅበራዊ ፡ ኩባንያዎች ፡ እንደ ፡ ኰሎናልፒ ፡ እንደ ፡ ሳቢያን ፡ ኰርፖሬሽን ፡ እንደ ፡ ትራንስፖርት ፡ ኮምፓኒ ፡ ያሉ ፡ ትልቅ ፡ ቤቶች ፡ ዲሬክተሮችና ፡ ቤቱን ፡ የተከራዩ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ሌሎችም ፡ ገንዘብ ፡ የተበደሩት ፡ ነጋዴዎች ፡ ይህንን ፡ ወሬ ፡ ሰምተው ፡ ስለመጡ ፡ በኦቶመቢል ፡ የአቃቂን ፡ ከተማ ፡ ሞልዋት ።

ወዲያው ፡ ከዚያች ፡ ከድሀ ፡ ጐጆ ፡ እናቱና ፡ ሶስት ፡ ካብታሞች ፡ ሰዎች ፡ ገቡ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ የፀሐይ ፡ መስፍንን ፡ ልጆች ፡ ታቅፎ ፡ በኃዘን ፡ ፊቱ ፡ ገርጥቶ ፡ እንባው ፡ እየወረደ ፡ ሲያለቅስ ፡ እናቱ ፡ ወይዘሮ ፡ በላይነሽ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ምን ፡ ሆንክ ፡ ምን ፡ መድኃኒት ፡ ነካህ ፡ እባክህ ፡ ልጄ ፡ ከዚህ ፡ ከድሀ ፡ ቤት ፡ ውስጥ በዶሮ ፡ ኩስና ፡ በመጥፎ ፡ ሽታ ፡ ቁጭ ፡ ብለህ ፡ የምታለቅስ ፡ ብለው ፡ ተቆጡት ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ በጣም ፡ ተቆጥቶ “ እናቴ ፡ ሆይ ፡ አሁን ፡ የመጣ ፡ ካብት ፡ ነውን ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ግፍ ፡ የሚያናግርሽ ፡ አባቴና ፡ አንቺ ፡ በዶሮ ፡ መነገድ ፡ አይደለምን ፡ ከዚህ ፡ የደረሳችሁት ፡ ይህች ፡ በኔ ፡ ግፍና ፡ ኃጢአት ፡ እንደ ፡ ሣር ፡ መንምና ፡ የሞተች ፡ የትልልቆች ፡ መሳፍንቶች ፡ ልጅ ፡ ኣልነበረችምን ፡ እኔ ፡ ክፉው ፡ ቤቴን ፡ እንዳታሳድፍ ፡ ለበዓል ፡ የተሰበሰቡት ፡ ወጣቶች ፡ በድኅነትዋ ፡ እንዳይጠየፉ ፡ ቀጠሮዬን ፡ አፍርሼ ፡ ካሽከሮች ፡ ቤት ፡ ዘግቼባት ፡ ከጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ መጽሐፍዋን ፡ ገልጣ ፡ ትታልኝ ፡ ሔደች ።

የጽሑፉም ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ሰው ፡ ሆይ ፡ ትላንት ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ካብታም ፡ የነበርክ ፡ ዛሬ ፡ ማነህ ፡ የተዋረድህ ፡ ድሀ ፡ አፈር ፡ ትቢያ ፡ አይደለህምን ፡ የሚል ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ ዘላለም ፡ ከልቤ ፡ ስለማይጠፋ ፡ ተመልሼ ፡ ቤቴን ፡ አላየውም ።

ወይዘሮ ፡ በላይነሽ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ንግግርና ፡ የኃዘን ፡ መልክ ፡ አይቼብህም ፡ አላውቅ ፡ ነበር ። በጣም ፡ የሚገርም ፡ ነው ፡ እባክህ ፡ ልጄ ፡ ተነሣ ፡ እንሒድ ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ከዚህ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አልሔድም ። አደራ ፡ የሰጠችኝን ፡ ልጆቹን ፡ አሳድጋለሁ ።

ወይዘሮ ፡ በላይነሽ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ምን ፡ ሆንክብኝ ፡ የማታውቃት ፡ ሴት ፡ ልጆችዋን ፡ አደራ ፡ ብትሰጥህ ፡ ባይሆን ፡ እንኳን ፡ ከቤትህ ፡ ወስደህ ፡ ታሳድጋለህ ፡ እንጂ ፡ ከዚህ ፡ ከበሰበሰ ፡ መንደር ፡ ለመኖር ፡

ታስባለህን ፡ እባክህ ፡ እንሂድ ፡ እያሉ ፡ ዕንባቸው ፡ ካይናቸው ፡ ይረግፍ ፡ ነበር ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታም ፡ የምወድሽ ፡ እናቴ ፡ እባክሽ ፡ ይቅር ፡ በይኝ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ጊዜ ፡ ከሚያጋጥመው ፡ ከፍ ፡ ካለ ፡ መከራ ፡ ጋር ፡ ደረት ፡ ለደረት ፡ ታግሎ ፡ ታሪኩን ፡ ለማሳመር ፡ የተፈጠረ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ የፀሐይ ፡ መስፍን ፡ አማሞት ፡ እኔን ፡ እንደ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ከማስቆጠሩም ፡ በስተቀር ፡ ይህቺ ፡ ሴት ፡ እኔን ፡ ለማግኘት ፡ መሥዋዕት ፡ ሆና ፡ መሞትዋ ፡ አይረሳኝም ።

ይልቁንም ፡ እኔን ፡ ለማግባት ፡ ስትል ፡ ልጆች ፡ የሉኝም ፡ ብላ ፡ ልጆችዋን ፡ መካድዋ ፡ ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ ታማ ፡ ከስታ ፡ ዓፅም ፡ መስላ ፡ እኔ ፡ መምጣቴን ፡ ብትሰማ ፡ የኔ ፡ ባልነት ፡ እንዳይቀርባት ፡ አጊጣ ፡ ተኲላ ፡ ወዳጄ ፡ በጎ ፡ ሆኘልሃለሁ ፡ እያለች ፡ ወደኔ ፡ የመጣችውን ፡ ስንኳን ፡ ሰውነቴ ፡ አጥንቴ ፡ አትረሳውም ።

ከቤቴም ፡ እንዳትገባ ። ንቂያት ፡ ገፍቻት ፡ አስቀይሚያት ፡ አሳዝኛ ፡ ስለሞተች ፡ የኮራሁበትን ፡ ቤት ፡ ተመልሼ ፡ አላየውም ፡

የውነተኛ ፡ ንስሐ ፡ እንዲሆነኝ ፡ ከዚሁ ፡ ልጆቼን ፡ እያሳደግሁ ፡ እኖራለሁ ፡ እናቴ ፡ እባክሽ ፡ ሒጂ ፡ አላት ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከዚያ ፡ የተሰበሰቡት ፡ ካብታሞች ፡ ሁሉ ፡ ራሳቸውን ፡ ይዘው ፡ እየጮሁ ፡ ምን ፡ መድኃኒት ፡ ነካው ፡ እያሉ ፡ ይደነቁ ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ካብቴ ፡ ፍሥሐ ፡ የሚባል ፡ የጥቅም ፡ ጓደኛው ፡ ምነው ፡ ወንድማችን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የተዘራውን ፡ ካብትህን ፡ ሳትሰበስብ ፡ ከዚች ፡ ጐጆ ፡ ውስጥ ፡ በመከራ ፡ እኖራለሁ ፡ ብለህ ፡ አልሔድም ፡ ትላለህ ፡ ስንት ፡ የምግባር ፡ አላፊነት ፡ ያለብህ ፡ ላንዲት ፡ ለማታውቃት ፡ ላላገባሃት ፡ ሴት ፡ እንደ ፡ ውሻ ፡ ባንዲት ፡ ጐጆ ፡ ውስጥ ፡ ህይወትህን ፡ ታሳልፋለህ ፡ በታሪክ ፡ ፊት ፡ እንደምን ፡ የሚያስቅ ፡ ይሆን ፡ እባክህ ፡ ወንድሜ ፡ እንሒድ ፡

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ስንኳን ፡ በጐጆ ፡ ውስጥ ፡ ባንዲት ፡ ሰባራ ፡ በርሜል ፡ ውስጥ ፡ ሕይወታቸውን ፡ ያሳለፉ ፡ ፈላስፎች ፡ ካንድ ፡ ንጉሥ ፡ ይበልጥ ፡ ታሪካቸው ፡ እስካሁን ፡ ያበራል ።

እኔ ፡ ግን ፡ ለዚህ ፡ አይደለም ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ በጣረሞት ፡ እጅዋን ፡ ተይዛ ፡ ስትጐተት ፡ ዘወር ፡ ብላ ፡ ልጆቼን ፡ አደራ ፡ ያለችኝ ፡ ድምፅ ፡ እስከ ፡ መቼም ፡ የማይረሳ ፡ ነገር ፡ ስለሆነ ፡ አልሔድም ።

አቶ ፡ ካብቴ ፡ ፍሥሐ ፡ የተወደድህ ፡ ወንድሜ ፡ ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ አለበረትህ ፡ ገብተህ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ የመሥዋዕትነት ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ማሰብህ ፡ በጣም ፡ ይገርማል ። ስለምን ፡ ያለወገንህ ፡ ከጨዋ ፡ ልጅ ፡ ሠፈር ፡ ገብተህ ፡ ገንዘብህንና ፡ ሕይወትህን ፡ ታጠፋለህ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ ባታውቀው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የጨዋ ፡ ልጅ ፡ የሚባል ፡ ስም ፡ የመልካም ፡ ሥራ ፡ ሠሪዎች ፡ ስም ፡ ነው ። ይህ ፡ ስም ፡ የተገኘው ፡ አያቶቻቸውና ፡ ቅድማያቶቻቸው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነጻነትና ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥታቸውን ፡ ክብር ፡ በደማቸው ፡ ካወጁት ፡ ከትልልቆች ፡ ሰዎች ፡ የተገኘ ፡ የሥራ ፡ ስም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ውጪ ፡ የሆነ ፡ የዘር ፡ ስም ፡ አይደለም ።

ለምሳሌ ፡ አባቱ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ቢኖረው ፡ ነጋዴ ፡ ወይም ፡ ካብታም ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ሀገሩ ፡ የመሥዋዕትነት ፡ ሥራ ፡ ሣይሠራ ፡ የጨዋ ፡ ልጅ ፡ አይባልም ።

የጨዋ ፡ ልጅነት ፡ የሚገኘው ፡ ከፍ ፡ ካለ ፡ መሥዋዕትነት ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ እበት ፡ ትል ፡ በማጠራቀም ፡ የጨዋ ፡ ልጅ ፡ አይባልም ።

ስለዚህ ፡ እኔ ፡ የድኃው ፡ ልጅ ፡ በዚህ ፡ ቁምነገሬ ፡ ከገፋሁበት ፡ ልጆቼን ፡ የጨዋ ፡ ልጅ ፡ አሰኛቸዋለሁ ።

ይልቁንስ ፡ ነገ ፡ ጠዋት ፡ አንድ ፡ ዳኛና ፡ የንስሐ ፡ አባቴን ፡ ጠበቃዬን ፡ ይዛችሁልኝ ፡ ነገ ፡ እንድትመጡ ፡ ብሎ ፡ አሰናበታቸውና ፡ ከናቱ ፡ ጋር ፡ እያለቀሱ ፡ ወደ ፡ እየቤታቸው ፡ ተመለሱ ።

# ምዕራፍ ፡ ፱ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ከጐረቤቶቹ ፡ ጋር ፡ ራቱን ፡ በልቶ ፡ ከዚያች ፡ ከድንክ ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ አንዲት ፡ ስስ ፡ ምንጣፍ ፡ አንጥፎ ፡ ልጆቹ ፡ እንዳይጐዱ ፡ ደህና ፡ ደህና ፡ ፍራሽና ፡ የብርድ ፡ ልብስ ፡ አስመጥቶ ፡ ባጠገቡ ፡ አስተኛቸው ።

መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ሲሆን ፡ ተስፋዬ ፡ የሚባለው ፡ ሕጻን ፡ እማማ ፡ እማማ ፡ እያለ ፡ ይጣራ ፡ ጀመር

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ የኔ ፡ ግፍና ፡ ጥጋብ ፡ ያመጣው ፡ መከራ ፡ ምን ፡ ያህላል ፡ ብሎ ፡ ተስፋዬን ፡ ከፍራሹ ፡ ላይ ፡ ኣንስቶ ፡ ታቅፎ ፡ አይዞህ ፡ እማማ ፡ ትመጣለች ፡ እያለ ፡ ከሳመው ፡ በኋላ ፡ ጡጦ ፡ እያጠባ ፡ አቅፎት ፡ ተኛ ።

በማግሥቱ ፡ ከማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ የርስት ፡ ክፍል ፡ ዋና ፡ ዲሬክተርና ፡ የንስሀ ፡ አባቱ ፡ ሦስት ፡ የጥቅም ፡ ጓደኞቹና ፡ ዋና ፡ ጠበቃው ፡ የርስቱና ፡ የገንዘቡ ፡ ጠቅላይ ፡ እንደራሴው ፡ ሆነው ፡ መጡ ።

ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ሰዎቹን ፡ ሁሉ ፡ አስወጥቶ ፡ ከተጠሩት ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ከዚያችው ፡ ከድሀ ፡ ጐጆው ፡ በብርጩማ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ኑዛዜውን ፡ ጀመረ ።

ካባቴ ፡ ያገኘሁትን ፡ ማናቸውንም ፡ ካብት ፡ ላሰለፈች ፡ ፀሐይነሽ ፡ ለውቢቱ ፡ ፀሐይነሽ ፡ ለተስፋዬ ፡ ፀሐይነሽ ፡ ሰጥቻለሁ ። ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ በኔ ፡ ስም ፡ ይጠሩ ። እናቴ ፡ አሉ ፡ ድረስ ፡ ከጠበቃዬና ፡ ከእንደራሲዬ ፡ ጋር ፡ እየተመካከሩ ፡ ሥራውን ፡ ያስኪዱ ፡ እነዚህ ፡ ልጆች ፡ አቅመ ፡ አዳም ፡ ከደረሱ ፡ ወዲያ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ሔደው ፡ ትምህርት ፡ እንዲማሩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ትምህርታቸውን ፡ ጨርሰው ፡ ዴግሪያቸውን ፡ ተቀብለው ፡ ሲመጡ ፡ ካብቴ ፡ እኩል ፡ ተከፍሎ ፡ ለልጆቼ ፡ ይሰጥ ። እኩሉ ፡ እናቴ ፡ እስከ ፡ ሞቱ ፡ ድረስ ፡ ይዘው ፡ ይገልገሉበት ፡ ካረፉ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ለልጆቼ ፡ ይሰጥ ፡ ብሎ ፡ ጽፎ ፡ ለማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ የርስት ፡ ዲሬክተር ፡ ፈርሞ ፡ ሰጠው

ከኑዛዜውም ፡ ላይ ፡ ዲሬክተሩና ፡ የንስሀ ፡ አባቱ ፡ ከፈረሙ ፡ በኋላ ፡ ለሥራ ፡ ጋደኞቹ ፡ እንደ ፡ እማኝ ፡ እንዲፈርሙ ፡ አቀረቡላቸው ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከጥቅም ፡ ጋደኞቼ ፡ አንዱ ፡ ወዳጄ ፡ ካብቴ ፡ የሚባለው ፡ ተነሥቶ ፡ በንደዚህ ፡ ባለ ፡ መሠረት ፡ በሌለው ፡ ቅዠት ፡ ኑዛዜ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ አልፈርምም ። ምነወ ፡ የኔ ፡ ወዳጅ ፡ አዋቂ ፡ ሰው ፡ አልነበርክምን ፡ እንደ ፡ ማታውቃት ፡ ሴት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከሕዝብ ፡ አታክልት ፡ ውስጥ ፡ አየኋት ፡ ብለህ ፡ አባትህ ፡ የደከመበትን ፡ ካብት ፡ ላልወለድካቸው ፡ ልጆች ፡ ታወርሳለህ ፡ ብሎ ፡ ተቆጣው ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ በማታውቀው ፡ ነገር ፡ ተቆጥተህ ፡ መናገርህ ፡ ያሳዝናል ፡ አንተ ፡ ዘወትር ፡ ገንዘብን ፡ ከሰው ፡ በላይ ፡ አድርገህ ፡ ትገምተዋለህ ።

ለኛ ፡ ለተማርነው ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ገንዘብ ፡ ለሰው ፡ ተፈጠረ ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ለገንዘብ ፡ እንዳልተፈጠረ ፡ እናምናለን ።

ገንዘባችንም ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ እንዳንሠራ ፡ ሊከለክለን ፡ አይችልም ።

ስለዚህ ፡ እኔ ፡ በፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ላይ ፡ ያለኝን ፡ የፍቅር ፡ ስሜትና ፡ እኔ ፡ እንደምን ፡ እንደ ፡ በደልኳት ፡ ሳታውቅ ፡ በከንቱ ፡ ትፈርዳለህ።

ወዳጄ ፡ ካብቴ ፡ ይሁን ፡ ለልጆቹስ ፡ አውርስ ፡ አንተ ፡ ምን ፡ በወጣህ ፡ ከዚህ ፡ ከድሀ ፡ ጐጆ ፡ ትቀመጣለህ ፡ ልጆችህን ፡ ይዘህ ፡ ከቤትህ ፡ አትሔድምን ፡

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ የቤቴ ፡ ምቹነትና ፡ ትልቅነት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግፍ ፡ ስላሠራኝ ፡ ዋና ፡ ጠላቴ ፡ ነው ።

ፀሐይ ፡ መስፍንን ፡ እኔው ፡ ጠርቻት ፡ በቀጠሮዋ ፡ ብትመጣ ፡ እንደ ፡ ጉዋደኞቼ ፡ የማታ ፡ ልብስ ፡ ስላለበሰች ፡ ካሽከር ፡ ቤት ፡ በማደርዋ ፡ በብስጭት ፡ ይህ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ በሽታ ፡ ወድቆባት ፡ በጭንቅና ፡ በሥቃይ ፡ ሞተች ።

ስለዚህ ፡ የውነተኛ ፡ ንስሐ ፡ የሚሆነኝ ፡ እስዋ ፡ በችግርና ፡ በስቃይ ፡ ከምትኖርበት ፡ ቤት ፡ መቀመጥ ፡ ነው ።

የኮራሁበትን ፡ ቤቴን ፡ እንደ ፡ ሎጥ ፡ ሚስት ፡ ዘወር ፡ ብዬ ፡ ሳየው ፡ የጨው ፡ ዓምድ ፡ እንደምሆን ፡ አይጠረጠርም ። ወንድሜ ፡ ሆይ እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ቤትህ ፡ ሒድ ፡ የኔና ፡ ያንተ ፡ አሳብ ፡ እንደ ፡ ሰማይና ፡ እንደ ፡ ምድር ፡ የተራራቀ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወዳጄ ፡ ካብቴና ፡ ሌሎችም ፡ የጥቅም ፡ ጋደኞቹ ፡ እናቱና ፡ ለማናዘዝ ፡ የመጡ ፡ ሹማምንቶቹ ፡ ከንስሐ ፡ አባቱ ፡ ጋር ፡ እያዘኑ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ተመለሱ ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታም ፡ ያደራ ፡ ልጆቹን ፡ ይዞ ፡ ከዚያው ፡ ከፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ቤት ፡ ተቀመጠ ። ከለመዱት ፡ መቃብር ፡ ይሞቃል ፡ እንደተባለው ፡ ከዚያች ፡ ከደሀ ፡ ጐጆ ፡ ውስጥ ፡ ዶሮቹን ፡ እያረባ ፡ ከልጆቹ ፡ ጋር ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ተቀመጠ ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ወዳጁ ፡ ፀሐይ ፡ መስፍን ፡ በሞተችበት ፡ ዕለት ፡ በሳምንት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አበባ ፡ ይዞ ፡ ሔዶ ፡ ከመቃብሩዋ ፡ ላይ ፡ አስቀምጦ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ጸሎቱን ፡ አድርጎ ፡ እንባውን ፡ አፍሶ ፡ ይመለስ ፡ ነበር ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ለዉዳጁ ፡ ለፀሐይ ፡ መስፍን ፡ በጣም ፡ የሚደንቅ ፡ የዕብነ ፡ በረድ ፡ መቃብር ፡ ቤት ፡ አሠራላት ፡

# ምዕራፍ ፡ ፲

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አሰለፈች ፡ ዓለሙ ፡ ውቢቱ ፡ ዓለሙ ፡ ተስፋዬ ፡ ዓለሙ ፡ ዓቅመ ፡ ዓዳም ፡ ስለ ፡ ደረሱና ፡ ያገራቸውን ፡ ትምህርት ፡ ንባብና ፡ ጽሕፈት ፡ ምግባርና ፡ ሃይማኖት ፡ ከተማሩ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ሔደው ፡ ዘመናዊውን ፡ ትምህርት ፡ እንዲማሩ ፡ ተማሪ ፡ ቤቱንና ፡ ገንዘቡን ፡ ካደራጀላቸው ፡ በኋላ ፡ ልጆቹን ፡ ጠርቶ ፡ እንደዚህ ፡ አላቸው ።

የተወደዳችሁ ፡ ልጆቼ ፡ ላባትና ፡ ለናት ፡ ዋና ፡ ደስታ ፡ ስማቸውን ፡ የሚያስጠሩ ፡ በሕዝብ ፡ ፊት ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ አስተያየት ፡ የተገመቱ ፡ ልጆች ፡ ያሉዋቸው ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ እኔን ፡ ደስ ፡ እንዲለኝና ፡ የናታችሁም ፡ ዓፅም ፡ እንዲለመልም ፡ አደራችሁን ፡ በመልካምነታችሁ ፡ ስማችንን ፡ አስጠሩ።

የጥበብ ፡ መጀመሪያ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ነውና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፍሩ ፡ ለወንድሞቻችሁ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ አድርጉ ። ትምርታችሁንም ፡ ለክፉ ፡ ነገር ፡ አታውሉት ። በገንዘብ ፡ ብዛት ፡ አትመኩ ። ገንዘብ ፡ በምግባርና ፡ በሃይማኖት ፡ ላይ ፡ ካልተመሠረተ ፡ ባሸዋ ፡ ላይ ፡ እንደተመሠረተ ፡ ቤት ፡ በነፋስና ፡ በጐርፍ ፡ ተመትቶ ፡ ፍርስርሱ ፡ ይወጣል ።

የተወደዳችሁ ፡ ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ እንደ ፡ ማቴሪያሊስቶችና ፡ እንደ ፡ ፍራማሶኖች ፡ ከሞትን ፡ በኋላ ፡ ፈርሰን ፡ በስብሰን ፡ እንቀራለን ፡ እንጂ ። የዘላለም ፡ ኑሮ ፡ የሚሆን ፡ ሌላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ የለም ፡ ብለው ፡ ኃጢአትን ፡ እንደ ፡ ልባቸው ፡ ለመሥራት ፡ እንዲመቻቸው ፡ ምግባርንና ፡ ሃይማኖትን ፡ ከመንገዳቸው ፡ ላይ ፡ አንሥተው ፡ ጥለው ፡ በሰፊ ፡ ጐዳና ፡ በክህደት ፡ እንደሚሔዱት ፡ ሰዎች ፡ እንዳትሆኑ ፡ ተጠንቀቁ ።

እግዚአብሔርን ፡ ብንክደው ፡ እኛ ፡ እንጐዳለን ፡ እንጂ ፡ ፡ እሱ ፡ በእግዚአብሔርነቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ።

የሰውም ፡ ልጅ ፡ ምንም ፡ ከሐዲ ፡ ቢሆን ፡ በመጨረሻው ፡ ጊዜ ፡ በጣር ፡ አልጋው ፡ ላይ ፡ ተጋድሞ ፡ ነፍሱ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ እርዳታ ፡ ለመፈለግ ፡ ዓይኑ ፡ ሲቅበዘበዝና ፡ ሰማይ ፡ ሰማይ ፡ ሲመለከት ፡ ይታያል ።

ለምሳሌ ፡ ስመ ፡ ጥሩው ፡ የፈረንሣዊ ፡ መንግሥት ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ክሊማንሶን ፡ ታሞ ፡ በጣር ፡ አልጋው ላይ ፡ ዓይኑ ፡ እየተንከራተተ ፡ ረዳት ፡ ሲፈልግ አንድ ፡ የሚወደው ፡ የሥራ ፡ ጓደኛው ፡ ሊያየው ፡ መጥቶ ፡ ከትራሱ አጠገብ ፡ ተጠግቶ ፡ ቆሞ ፡ ሊያጽናናው ፡ ዛሬስ ፡ ተሽሎሃል ፡ ልትድን ፡ ይመስለኛል ፡ አለው ። ክሊማንሶንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ሊያውቅ ፡ አይችልም ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የሥራ ፡ ጓደኛውና ፡ ታስታምመው ፡ የነበረች ፡ ሲስተር ፡ ደንግጠው ፡ ከተመለከቱት ፡ በኋላ ፡ ሲስቴርዋ ፡ ክቡር ፡ ሆይ ፡ ሰምቼብህ ፡ የማላውቀውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ እምነት ፡ ካንተ ፡ በመስማቴ ፡ በጣም ፡ ገረመኝ ፡ አለችው ።

ክሊማንሶንም ፡ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ የውነት ፡ መናገሪያዬ ፡ ጊዜው ፡ ስለ ፡ ደረሰ ፡ ነው ። ብልዋት ፡ ወዲያው ፡ ዓረፈ ፡ ይባላል ።

ስለዚህ ፡ ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ በመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ እረዳት ፡ ከመፈለግና ፡ ዓይንን ፡ ካልጋ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ከማንከራተት ፡ አሁኑኑ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አምኖ ፡ የሰላም እንቅልፍ ፡ ማንቀልፋት ፡ ስለውል ፡ ሃይማኖታችሁንና ፡ ምግባራችሁን ፡ በጭንጫ ፡ ላይ ፡ መሥርቱ።

ከዚህ ፡ በስተቀር ፡ የምመክራችሁ ፡ እኔ ፡ አባታችሁ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ትቼላችኋለሁና ፡ ገንዘባችሁ ፡ ባልሆነው ፡ ገንዘብ ፡ ወዳጅ ፡ ግዞበት ፡ ያለውን ፡ የመድኃኒታችንን ፡ ቃል እያሰባችሁ ፡ ገንዘቤን ፡ ስማችሁን ፡ በሚያስጠራ ፡ ሥራ ፡ አውሉት ፡

እኔ ፡ በናታችሁ ፡ ኃዘን ፡ ቤቴንና ፡ ድሎቴን ፡ ትቼ ፡ በመሔዴ ፡ በቁም ፡ ነገሬ ፡ ስሜን ፡ በጨዋ ፡ ልጅነት ፡ አሰይሜዋለሁና ፡ እናንተም

፡ ልጆቼ ፡ በኔም ፡ በናታችሁም ፡ ባያት ፡ በቅድማያታችሁም ፡ በቁም ፡ ነገር ፡ ሥራ ፡ የጨዋ ፡ ልጆች ፡ ናችሁና ፡ ጨዋነታችሁን ፡ አትርሱ ።

ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ እናቴን ፡ አያታችሁን ፡ አደራ ፡ ውደድዋት ፡ አስቡላት ፡ እግዚአብሔር ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ መርቆ ፡ እቅፍ ፡ አድርጎ ፡ ስሞ ፡ ኣሰናበታቸውና ፡ እንባው ፡ ይረግፍ ፡ ጀመር ።

ልጆቹም ፡ እንደናት ፡ ጡጦ ፡ እያጠባ ፡ ካሳደጋቸው ፡ አባታቸው ፡ ሲለያዩ ፡ መሪር ፡ የሆነ ፡ ለቅሶ ፡ እያለቀሱ ፡ ከልጅ ፡ ዓለሙ ፡ እንደራሴ ፡ ጋር ፡ በአሮይፕላን ፡ እንዲያሳፍራቸው ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሔዱ

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ግን ፡ ከዚያው ፡ ከባዶ ፡ ቤት ፡ ብቻውን ፡ ዘግቶ ፡ ጐረቤቶቹም ፡ እንዳይመጡበት ፡ ከበራፉ ፡ ላይ ፡ በጉልህ ፡ ጽሕፈት ፡ ከዚህ ፡ ቤት ፡ መግባት ፡ ክልክል ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ማስታወቂያ ፡ ለጥፎ ፡ ቀን ፡ ቀን ፡ መጻሕፍቶቹን ፡ ይመለከት ፡ ነበር

ከሌሊቱ ፡ በ፯ ፡ ሰዓት ፡ ልብን ፡ በሚመታ ፡ የልቅሶ ፡ ዜማ ፡ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ ያዜም ፡ ነበር ።

ብፈልግ ፡ አጣኋት ፡ ካአሽከሮቼ ፡ ቤት ፡  
ፀሐይቱ ፡ መስፍን ፡ የውነት ፡ ወይዘሪት ፤  
ምነስ ፡ ብትዋረድ ፡ ብትወድቅ ፡ ከመሬት ፤  
ባባትዋ ፡ መስፍን ፡ ናት ፡ በናትዋ ፡ እመቤት፤  
ዋኔን ዋኔን ፡ እኔ ፡ አፈር ልሁን ፡

****

በዚያ ፡ በዝናም ጐርፍ ፡ በሚያስፈራ ፡ ሌት ፡  
ብቻዋን ፡ ስትሮጥ ፡ ልጅዋን ፡ ለማየት  
ስትወድቅ ፡ ስትነሣ የሰማዩ ፡ ቁጣ ፡ እንደ ፡ ቦምብ ሲበርቅ ደረሰች ፡  
አቃቂ ፡ በአሳር ፡ በጭንቅ ፤  
ዋኔን ፡ ዋኔን ፡ እኔ ፡ አፈር ፡ ልሁን ።

*****

ቆረጠች ፡ ለመውደቅ ፡ እባሕሩ ፡ ላይ ፡
ተስፋዬን ፡ ከመሬት ፡ ወድቆ ፡ እንዳታይ ፤
ወዳጄ ፡ ፀሐይነሽ ፡ ላይሽ ፡ መጣሁኝ ፡
ታመሻል ፡ የሚሉ ፡ ስለሰማሁኝ ፤
ዋኔን ፡ ዋኔን ፡ እኔ ፡ አፈር ፡ ልሁን ።

*****

ኣንቺ ፡ ግን ፡ ለሠርግሽ ፡ መጣሽ ፡ አጊጦሽ ፡
ዓይንሽን አየሁት ፡ ሞትን ፡ ተኩለሽ ፤
ዘወትር ፡ የማይሽር ፡ የልብ ፡ ነቀርሳ ፤
በኔ ፡ የደረሰው ፡ የነፍስ ፡ ወቀሳ ፤
ደህና ፡ ስንብት ፡ አልሽኚ ፡ ልጆቼን ፡ ስጥተሽ ፤
እኔ ፡ እንዳንቺ ፡ ሆኜ ፡ የማልሞት ፡ መስሎሽ ፤
ዋኔን ፡ ዋኔን ፡ እኔ ፡ አፈር ፡ ልሁን ።

*****

እያለ ፡ የለቅሶ ፡ ዜማ ፡ ሲያንጐራጉር ፡ ጐረቤቶቹ ፡ ሁሉ ፡ እየተደበቁ ፡ ከቤቱ ፡ አጠገብ ፡ ቀርበው ፡ የለቅሶውን ፡ ዜማ ፡ እየሰሙ ፡ እነሱም ፡ ያለቅሱ ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በስምንተኛው ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ የለቅሶውን ፡ ዜማ ፡ ለመስማት ፡ ቢሔዱ ፡ ምንም ፡ ድምፅ ፡ አልሰሙም ፡ በማግስቱም ፡ በሳልስቱም ፡ ምንም ፡ የልቅሶ ፡ ዜማ ፡ ሳይሰሙ ፡ ቀሩ።

በአራተኛው ፡ ቀን ፡ ምን ፡ ሆኖ ፡ ይሆን ፡ ብለው ፡ በሩን ፡ ቢመቱት ፡ ቁልፉንም ፡ ቢያዞሩ ፡ ቢጣሩም ፡ መልስ ፡ አጡ ።

ስለዚህ ፡ ሔደው ፡ ለአገረ ፡ ገዥው ፡ ክቡር ፡ ሆይ ፡ ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ የሚባለው ፡ ሰው ፡ ልጆቹን ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ለትምህርት ፡ ከሰደደበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ቤቱን ፡ ዘግቶ ፡ ብቻውን ፡ በኩለሌሊት ፡ የሚያሳዝን ፡ የልቅሶ ፡ ዜማ ፡ ያዜም ፡ ነበር ።

አሁን ፡ ግን ፡ ይኸው ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ይሆነዋል ። ከደጅም ፡ ኣይወጣ ፡ ከውስጥም ፡ ድምጹ ፡ ኣይሰማም ።

ስለዚህ ፡ ክቡርነትዎ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሔደው ፡ በርስዎ ፡ ፊት ፡ በሩን ፡ ሰብረን ፡ ብንገባና ፡ ሞቶም ፡ እንደሆነ ፡ ብንቀብረው ፡ የተሻለ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ስላስታወቁት ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ሔዶ ፡ በኃይል ፡ በሩን ፡ ገፍተው ፡ ሰብረው ፡ ቢገቡ ፡ ምንም ፡ ሰው ፡ አላገኙም ። ከፎቁም ፡ ላይ ፡ ወጥተው ፡ ቢፈልጉ ፡ ከመኝታው ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ አንዲት ፡ ግጥም ፡ የተጻፈባት ፡ ወረቀት ፡ ብቻ ፡ አገኙ ። ቃሉም ፡ ይህ ፡ ነው ።

ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ዘመዱ ፡

መች ፡ ይሸኛል ፡ ወዳጅ ፡ እርቀው ፡ ሲሔዱ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ ጽሑፉን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሒዶ ፡ አገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስትር ፡ ሰጥቶ ፡ የሆነውን ፡ ታሪክ ፡ ሁሉ ፡ ነገረው ።

ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስትር ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ እንዲፈለግ ፡ ትእዛዝ ፡ አሳለፈ ።

ነገር ፡ ግን ፡ በየአውራጃውና ፡ በየምስለኔው ፡ በየደብሩና ፡ በየገዳሙ ፡ ተፈልጎ ፡ ምንም ፡ ምልክት ፡ አልተገኘም ። ስለዚህ ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ሕዝብ ፡ የልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታን ፡ የቆራጥነትና ፡ የቁም ፡ ነገር ፡ ሥራ ፡ ሰምተው ፡ ስለነበረ ፡ በመጥፋቱ ፡ በጣም ፡ አዘኑ ። ሰሞኑን ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ ጫወታ ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ ጫወታ ፡ ሕዝቡ ፡ አይጫወትም ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በጊዜ ፡ ምክንያት ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ እየተረሳ ፡ ሔደ ።

የልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታም ፡ ልጆች ፡ ሎንዶን ፡ በሔዱ ፡ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ ትምህርታቸውን ፡ ጨርሰው ፡ ዲግሪያቸውን ፡ ተቀብለው ፡ መጡ ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ በገቡ ፡ በሦስተኛው ፡ ወር ፡ የልጅ ፡ ዓለሙ ፡ እናት ፡ አያታቸው ፡ ሞተው ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ወስደው ፡ ቀበርዋቸው ።

# ምዕራፍ ፡ ፲፩ ፡

የልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ልጆች ፡ ያያታቸውንና ፡ ያባታቸውን ፡ ካብት ፡ ወርሰው ፡ በካብትም ፡ በእውቀትም ፡ በመንፈስም ፡ በምግባርና ፡ በሃይማኖትም ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ወጣቶች ፡ ሆኑ ።

ታላቂቱ ፡ አሰለፈች ፡ ዓለሙ ፡ በጤና ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ ዋና ፡ ዲሬክተርነት ፡ ተሾመች ።

ውቢቱ ፡ ዓለሙ ፡ የንግድ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ አስተማሪነት ፡ ተሾመች።

ተስፋዬ ፡ ዓለሙ ፡ በውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ የክፍል ፡ ዲሬክተርነት ፡ ተሾመ ። እነዚህ ፡ ሦስት ፡ የመልካም ፡ ዛፍ ፡ ፍሬዎች ፡ ያባታቸውንና ፡ ያያታቸውን ፡ የቅድማያታቸውን ፡ ስም ፡ በመልካም ፡ አስጠሩ

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ታናሻቸው ፡ ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ ዓለሙ ፡ እኅቶቹን ፡ ሰብስቦ ፡ የተወደዳችሁ ፡ እህቶቼ ፡ አባታችን ፡ ለትምህርት ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ሲሰደን ፡ ገንዘብ ፡ በምግባርና ፡ በሃይማኖት ፡ ላይ ፡ ካልተመሠረተ ፡ ባሸዋ ፡ ላይ ፡ እንደተገነባ ፡ ቤት ፡ በነፋስና ፡ በጐርፍ ፡ ተመትቶ ፡ ፍርስርሱ ፡ ይወጣል ፡ ያለንን ፡ መርሳት ፡ አይገባንም።


ስለዚህ ፡ ገንዘባችንና ፡ ካብታችንን ፡ ከጭንጫ ፡ ላይ ፡ እንድንመሠርት ፡ ባባታችን ፡ በልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ስም ፡ አንድ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ለሕዝብ ፡ እርዳታ ፡ የሚሆን ፡ እንሥራ ፡ ብሎ ፡ አስታወቃቸው።

እኅቶቹም ፡ ይኸንን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ያሳሰባቸውን ፡ ወንድማቸውን ፡ አመስግነው ፡ የሚሠሩትን ፡ ሥራ ፡ ይመካከሩ ፡ ጀመር።

አሰለፈች ፡ ዓለሙ ፡ አንድ ፡ የድሆች ፡ ሆስፒታል ፡ እንሥራ ፡ አለች።

ውቢቱ ፡ ዓለሙ ፡ እንደኔ ፡ ሐሳ ብ ፡ እናት ፡ አባታቸው ፡ ለሞቱባቸው ፡ ሕጻናቶች ፡ ማሳደጊያ ፡ እንሥራ ፡ አለች ።

ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ ዓለሙ ፡ እኅቶቼ ፡ የኔ ፡ ምርጫ ፡ ከናንተ ፡ የተሻለ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ አይደለም ፡



የልጅ ፡ ዓለሙ ፡ የሽማግሌዎች መጦርያ ፡ ሆስፒታል ።

እንደኔ ፡ ሐሳብ ፡ ዘመድና ፡ ጠዋሪ ፡ ልጅ ፡ የሌላቸውን ፡ ሽማግሎች ፡ መጦሪያ ፡ ቤት ፡ ብናቆም ፡ ይሻል ፡ ይመስለኛል ። ምክንያቱም ፡ አንድ

፡ ሽማግሌ ፡ የገዛ ፡ አካላቱ ፡ አልታዘዝ ፡ ሲለው ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሊወደው ፡ ሊታዘዘው ፡ አይፈቅድም ።

ዘወትር ፡ የሰውን ፡ እርዳታ ፡ ሲፈልግ ፡ ዓይኑ ፡ ሲንከራተት ፡ ያሳዝነኛል ። ልጆች ፡ ስንኳን ፡ ቢኖሩት ፡ ሁሉም ፡ የዕለት ፡ ኑሮዋቸውን ፡ ሲፈልጉ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ሲውሉ ፡ ሽማግሌው ፡ ሲርበው ፡ መብል ፡ ሲጠማው ፡ መጠጥ ፡ አያገኝም ። እውጪ ፡ ከፀሐይ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ጀርባውን ፡ ፀሐይ ፡ እያስመታ ፡ የኔ ፡ ዕድሜ ፡ የዕድሜ ፡ አተላ ፡ ነው ፡ እያለ ፡ የቀድሞውን ፡ ጉብዝናውንና ፡ ባልንጀሮቹን ፡ እያሰበ ፡ ያለቅሳል።

ልጅና ፡ ዘመድ ፡ የሌለው ፡ ሽማግሌማ ፡ እንደምን ፡ ያለ ፡ ጭንቅ ፡ ይደርስበት ። ስለዚህ ፡ የኔን ፡ አሳብ ፡ ብትቀበሉኝ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ አላቸው ።

ሁለቱም ፡ እኅቶቹ ፡ የተወደድህ ፡ ወንድማችን ፡ ያንተኑ ፡ አሣብ ፡ ተቀብለናል ፡ ከዚህ ፡ የተሻለ ፡ ምርጫ ፡ አይገኝም ። ተባብለው ፡ የሽማግሌዎች ፡ መጦሪያ ፡ ቤት ፡ ለመሥራት ፡ ቆረጡ ።

ሦስቱም ፡ ልጆች ፡ ከየገንዘባቸው ፡ አዋጥተው ፡ ለመቶ ፡ ሽማግሌዎች ፡ የሚበቃ ፡ አልጋ ፡ ያለው ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ሆስፒታል ፡ ሠሩ።

ድርጅቱን ፡ ሁሉ ፡ በገዛ ፡ ገንዘባቸው ፡ በመልካም ፡ አከናወኑ ። ስሙንም ፡ የልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ሆስፒታል ፡ ብለው ፡ ሰየሙት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ጠዋሪ ፡ የሌላቸው ፡ ሽማግሌዎች ፡ ከሸዋ ፡ ከትግሬ ፡ ከጐጃም ፡ ከጋላውም ፡ አገር ፡ እየመጡ ፡ ገቡበት ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ ዓለሙ ፡ ሆስፒታሉን ፡ ለመጐብኘትና ፡ የጐደለውንም ፡ ነገር ፡ ለመጠየቅ ፡ መጥቶ ፡ ከሽማግሌ ፡ መቀበያው ፡ ቢሮ ፡ ሲገባ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በጣም ፡ የከሳ ፡ ዓፅም ፡ የሚመስል ፡ ዘመድ ፡ ልጅ ፡ የሌለኝ ፡ ሽማግሌ ፡ ነኝና ፡ ተቀበሉኝ ፡ እያለ ፡ ሲጮህ ፡ የሽማግሌ ፡ መቀበያው ፡ የቢሮ ፡ ሹም ፡ አንተ ፡ በሕመም ፡ ምክንያት ፡ ከስተሃል ፡ እንጂ ፡ ሽማግሌ ፡ አይደለህም ፡ ስለዚህ ፡ በተሰጠን ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ልንቀበልህ ፡ አንችልም ፡ እያሉ ፡ ሲገፉት

፡ ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ አይቶት ፡ በጣም ፡ አዘነለትና ፡ ወደሰውዬው ፡ ቀርቦ ፡ ስንት ፡ ዓመትዎ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ።

ሰውዬውም ፡ ስልሳ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ይሆነኛል ፡ ብሎ ፡ መለሰለት።

ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ ጠዋሪ ፡ ልጅ ፡ የለዎትምን ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ሰውዬውም ፡ ስንኳን ፡ ልጅ ፡ ዘውድም ፡ የለኝም ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ ዓለሙ ፡ ልጅ ፡ ከሌለው ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ በጣም ፡ የሚያሳዝን ፡ ነውና ፡ ተቀበሉት ፡ ለምግቡ ፡ እኔ ፡ በተለየ ፡ እከፍልለታለሁ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ጡረታ ፡ አስገባው ።

ሰውዬው ፡ በጣም ፡ ስለተጐዳና ፡ ስለደከመ ፡ ወዲያው ፡ ካልጋ ፡ ላይ ፡ አስተኙት ።

በማግስቱ ፡ ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ ዓለሙ ፡ እኅቶቹን ፡ በኔ ፡ ሐሳብ ፡ ከሽማግሌ ፡ መጦሪያ ፡ ቤት ፡ ያገባሁትን ፡ ሰው ፡ ብታዩት ፡ በጣም ፡ ታዝናላችሁ ። መልኩ ፡ እጅግ ፡ የሚያምር ፡ ንግግሩ ፡ የረቀቀ ፡ አጥንት ፡ ሰብሮ ፡ የሚገባ ፡ ነው ። አከሳሱ ፡ ግን ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ሰው ፡ ነው ። እባካችሁ ፡ እንሒድና ፡ እንየው ፡ አላቸው

እኅቶቹም ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ይለናል ። ብለው ፡ ከወንድማቸው ፡ ጋር ፡ ሔዱ ።

ወዲያው ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ ከመኝታ ፡ ቤቱ ፡ ገብተው ፡ አዩትና ፡ ስለከሳቱና ፡ ስለሕመሙ ፡ ይልቁንም ፡ በመልኩ ፡ ርቀትና ፡ በንግግሩ ፡ ደስ ፡ ማሰኘት ፡ ዕንባቸው ፡ ይፈስ ፡ ጀመር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሁለቱም ፡ እኅቶቹ ፡ እንደ ፡ ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ በጣም ፡ ስለወደዱትና ፡ ስላዘኑለት ፡ ከሳምንት ፡ ሁለት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ አታክልትና ፡ ፍሬ ፡ ይዘውለት ፡ ይመጡ ፡ ነበር ።

ልጅ ፡ ተስፋዬም ፡ የሚሞቀው ፡ ልብስና ፡ ሌላም ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ ያመጣለት ፡ ነበር ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሦስቱም ፡ ልጆች ፡ አንዳንድ ፡ የሚበላ ፡ ነገር ፡ ይዘውለት ፡ መጥተው ፡ ሲሰጡት ፡ ጌቶቼ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጥልኝ ፡ ፈቃዳችሁ ፡ ቢሆን ፡ ሁለት ፡ ሦስት ፡ ደቂቃ ፡ ያህል ፡ የማጫውታችሁ ፡ ጉዳይ ፡ አለና ፡ ጠጋ ፡ ብላችሁ ፡ ከወንበር ፡ ላይ ፡ ተቀመጡ ፡ አላቸው ።

እነሱም ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ይለናል ፡ ብለው ፡ ሦስቱም ፡ ካልጋው ፡ ተጠግተው ፡ በወንበር ፡ ላይ ፡ ተቀመጡ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሽማግሌው ፡ ንግግሩን ፡ ጀመረ። ጌቶቼ ፡ ሆይ ፡ ለኔ ፡ ከዚህ ፡ ከሽማግሌ ፡ መጠሪያ ፡ ቤት ፡ ማግባታችሁ ፡ ብቻ ፡ ይበቃኛል ። ከዚህ ፡ በስተቀር ፡ ትርፍ ፡ ነገር ፡ ይዛችሁ ፡ አትምጡ ። ምክንያቱም ፡ ለኔ ፡ ትርፍ ፡ ነገር ፡ ስታደርጉ ፡ የአድልዎ ፡ ኃጢአት ፡ ልትሠሩ ፡ ነው ። በኔ ፡ ምክንያት ፡ ባጠገቤ ፡ ያሉ ፡ ሽማግሌዎች ፡ የቅናት ፡ መንፈስ ፡ ሊያድርባቸው ፡ ነው ፡

ስለዚህ ፡ ለመጠቀሚያ ፡ ያደረጋችሁት ፡ ሰፊ ፡ ችሮታ ፡ ለጉዳት ፡ እንዳይሆን ፡ ለኔ ፡ ብቻ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ አታድርጉልኝ ። ጌቶቼ ፡ ሆይ ፡ እንዲያውም ፡ የምመክራችሁ ፡ ከዚህ ፡ ድሆችን ፡ ለመጐብኘት ፡ ስትመጡ ፡ አጊጣችሁ ፡ ኣምራችሁ ፡ አትምጡ ። ለድሆች ፡ መጐብኛ ፡ ተራ ፡ ልብስ ፡ ገዝታችሁ ፡ አስቀምጡ ።

የተከበራችሁ ፡ ጌቶቼ ፡ ሆይ ፡ እነዚህ ፡ ገንዘባችሁን ፡ አውጥታችሁ ፡ የምትጠርዋቸው ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሁሉ ፡ ምነው ፡ እንደነዚህ ፡ ልጆች ፡ አምሮብን ፡ አጊጠን ፡ ብንሞት ፡ የሚል ፡ የምኞት ፡ ኃጢአት ፡ ይነሣባቸዋል ።

ስለዚህ ፡ እናንትም ፡ በነዚህ ፡ በድሆች ፡ ፊት ፡ አምራችሁ ፡ ገናችሁ ፡ ሠራተኞች ፡ ሁሉ ፡ ሰላምታ ፡ ሲሰጡዋችሁና ፡ ሽማግሌዎችም ፡ ዓይናቸውና ፡ ተስፋቸው ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ስታዩ ፡ የኩራት ፡ መንፈስ ፡ ያድርባችሁና ፡ ዋጋችሁ ፡ ይኸው ፡ ምስጋና ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ይቀራል ። ስለዚህ ፡ መድኃኒታችን ፡ ገንዘባችሁ ፡ ባልሆነው ፡ ገንዘብ ፡ ወዳጅ ፡ ግዙበት ። እንዳለው ፡ ሁሉ ፡ እናንተም ፡ ገንዘባችሁ ፡ ባልሆነ

፡ ገንዘብ ፡ አንዳንድ ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ መስላችሁ ፡ አስተዳድሩ ፡ እንጂ ፡ ባኳኋናችሁ ፡ ጌቶች ፡ መስላችሁ ፡ አትታዩ ።

ቀኝህ ፡ የሚሠራውን ፡ ግራህ ፡ አይየው ፡ ተብሎ ፡ ተጽፍዋል ፡ ብሎ ፡ መከራቸው ።

# መዕራፍ ፡ ፲፪ ፡፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሶስቱም ፡ ልጆች ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ምክር ፡ ስለሰጡን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጥዎ ፡ ከዛሬ ፡ ጀምረን ፡ ያሽከሮች ፡ ልብስ ፡ ዓይነት ፡ ካኪ ፡ እናሰፋለን ። ለሚጦሩትም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ምንም ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ ሳናደርግ ፡ ሁሉንም ፡ የተቻለንን ፡ ያህል ፡ ደስ ፡ አሰኝተን ፡ እንጦራቸዋለን ፡ አልዋቸው ።

ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ እባክዎ ፡ አባቴ ፡ ከፈረንጅ ፡ አገር ፡ ሔደው ፡ ተምረዋልን ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ።

ሰውዬውም ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ከፈረንጅ ፡ አገር ፡ ያየሁኝ ፡ መሰለህ/

ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ ለዚህ ፡ አይደለም ፡ ንግግርዎ ፡ ከፈረንጅ ፡ አገር ፡ የተማሩ ፡ ስለመሰለኝ ፡ ነው

ሽማግሌው ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ መልክ ፡ የተፈጠረ ፡ ክፉና ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ ለማወቅ ፡ ከፈረንጅ ፡ አገር ፡ መሔድ ፡ አያስፈልገውም ።

ከፈረንጅ ፡ አገር ፡ መሔድ ፡ የሚጠቅመው ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ እንዲችል ፡ እውቀቱን ፡ ለማሻሻል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለምግባርና ፡ በጎ ፡ ሥራን ፡ ለመሥራት ፡ አገሩ ፡ ላይ ፡ ሁሉንም ፡ ለማወቅ ፡ ይችላል ።

የበጎም ፡ ሥራ ፡ መሠረቱ ፡ አጭር ፡ ነው ።

ላንተ ፡ ቢያደርግልህ ፡ የምትወደውን ፡ እንደዚሁም ፡ ለወንድምህ ፡ አድርግ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ የሲያንስ ፡ የኰኖሚ ፡ ፖለቲክ ፡ የሕግ ፡ የማዕድን ፡ የመሐንዲስ ፡ ይህንን ፡ የመሰሉ ፡ ጥበቦች ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ ካልተመሠረቱ ፡ ነፍስ ፡ እንደ ፡ ሌለው ፡ ሥጋ ፡ ይሆናሉ ። ነፍስ ፡ የሌለው ፡ ሥጋ ፡ ለወገኑ ፡ ምንም ፡ እንደማይጠቅም ፡ ምግባርና ፡

ሃይማኖት ፡ የሌላቸው ፡ አዋቂዎት ፡ ለሀገራቸው ፡ እንደማይጠቅሙ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

አንድ ፡ ሰው ፡ ላንድ ፡ ሊቅ ፡ ወዳጅህን ፡ ታምነዋለህን ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ አወን ፡ እሱ ፡ እግዚእብሔርን ፡ ስለሚያምን ፡ እኔም ፡ እሱን ፡ በጣም ፡ አምነዋለሁ ። አለው ፡ ይባላል ።

ባገራችንም ፡ ምሳሌ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከማይፈራ ፡ ወዳጅህ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ ጠላትህ ፡ ይሻልሃል ፡ ተብልዋል ።

ምግባርና ፡ ሃይማኖት ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ዋስና ፡ ተያገሮች ፡ ናቸው።

ስለዚህ ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ የምግባርና ፡ የሃይማኖትን ፡ ትምህርት ፡ ከዚሁ ፡ ካገሬ ፡ ላይ ፡ ካባቴና ፡ ከናቴ ፡ መልካም ፡ አስተዳደግ ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ ያገኘሁት

መልካም ፡ ቤተሰቦች ፡ እንዳንድ ፡ ኡኒቬርሲቲ ፡ ኰሌጅ ፡ ይቆጠራሉ።

ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ እርሰዎን ፡ ከዚህ ፡ ሆስፒታል ፡ እንዲጠሩ ፡ ያመጣልንን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እናመሰግናለን ። ምክንያቱም ፡ እርስዎን ፡ ለመጠየቅ ፡ በመጣን ፡ ቁጥር ፡ አጥንት ፡ ሰብሮ ፡ የሚገባ ፡ መልካም ፡ ምክርዎን ፡ በመስማት ፡ ዘወትር ፡ ሰውነታችንን ፡ አድሰን ፡ ምን ፡ መሆናችንን ፡ አውቀን ፡ እንሔዳለን ። እግዚአብሔር ፡ ዋጋዎን ፡ ይክፈልዎ ፡ አላቸው ።

ሽማግሌውም ፡ ዋጋዬንማ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፍሎኝ ፡ ከናንተ ፡ አገናኝቶኝ ፡ በመልካም ፡ እጦራለሁ ። እንግዲህ ፡ ሒዱ ፡ ጌቶቼ ።

እነሱም ፡ ተነስተው ፡ ተሰናብተው ፡ ወጡ ። ሲሔዱም ፡ መንገድ ፡ ለመንገድ ፡ የሽማግሌውን ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ ገርምዋቸው ፡ ይጫወቱ ፡ ነበር ።

ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ ዓለሙ ፡ እኚህ ፡ ሽማግሌ ፡ ፈረንጅ ፡ አገር ፡ ሔደው ፡ የተማሩ ፡ ናቸው ። አልሔድኩም ፡ ቢሉኝም ፡ አላምንም ።

እንዲያውም ፡ ከኡኒቬርሲቴ ፡ የወጡና ፡ የፊሊዞፊም ፡ ትምህርት ፡ ያጠኑ ፡ ዋና ፡ ሊቅ ፡ ይመስሉኛል ።

ውቢቱ ፡ ዓለሙ ፡ እርግጥ ፡ ንግግራቸው ፡ በትምህርት ፡ የበሰሉ ፡ ናቸው ። ይልቁንም ፡ በቲዮሎጂ ፡ ትምህርት ፡ በኲል ፡ ሊቅ ፡ መሆናቸው ፡ ይታያል ። ነገር ፡ ግን ፡ ባገራችንም ፡ ብዙ ፡ ሊቃውንቶች ፡ በቲዮሎጂ ፡ ትምህርት ፡ በኲል ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ሊቃውንቶች ፡ አውቃለሁ።

አሰለፈች ፡ ዓለሙ ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ ባገራችንም ፡ በጣም ፡ የተማሩ ፡ ሰዎች ፡ ይገኛሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ እኚህ ፡ ሽማግሌ ፡ የኡኒቬርሲቴ ፡ የፊሊዞፊ ፡ መምህር ፡ ይመስሉኛል ። ብዙ ፡ ባገራችን ፡ ትምህርት ፡ በጣም ፡ የጠለቀ ፡ ትምህርት ፡ ያላቸው ፡ ሊቆች ፡ ቢኖሩም ፡ እንደኚህ ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡ የላቸውም ፡ እየተባባሉ ፡ አሳብ ፡ ላሳብ ፡ ከተለዋወጡ ፡ በኋላ ፡ ሁሉም ፡ ወደ ፡ እየሥራቸው ፡ ሔዱ ።

# ምዕራፍ ፡ ፲፫ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሽማግሌው ፡ ታመሙ ። ስለዚህ ፡ ሶስቱም ፡ ልጆች ፡ እጅግ ፡ ተጨነቁ ። ምክንያቱም ፡ አንዳንድ ፡ ቀን ፡ እሳቸውን ፡ ለማየት ፡ በሔዱ ፡ ጊዜ ፡ ምክራቸውና ፡ ጫወታቸው ፡ አጥንት ፡ ሰብሮ ፡ የሚገባ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። ከሳቸውም ፡ ዘንድ ፡ መሔድ ፡ ልክ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሔዶ ፡ መጽሐፍን ፡ እንደ ፡ መስማት ፡ ይቆጥሩት ፡ ነበር ።

ስለ ፡ ሕመማቸውም ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ያሉትን ፡ ሐኪሞች ፡ ሁሉ ፡ ሰብስበው ፡ ምርመራ ፡ ተደረገላቸው

ነገር ፡ ግን ፡ የምርመራው ፡ ውጤት ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ተስፋ ፡ አልሰጠውም ። ሐኪሞቹ ፡ ሁሉ ፡ እኒህ ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ በኃዘን ፡ ምክንያት ፡ ሰውነታቸው ፡ እንደተመታ ፡ ይታያል ። ምክንያቱ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ አይታወቅም ።

ሁለተኛው ፡ በሕመም ፡ ምክንያት ፡ ሳይሆን ፡ በገዛ ፡ ፈቃዳቸው ፡ እህል ፡ ውሀ ፡ ትተው ፡ ሰውነታቸውን ፡ ገለውታል ። ከመድከምና ፡ ከመጐዳት ፡ በስተቀር ፡ አንድም ፡ የሕመም ፡ ምክንያት ፡ አላገኘንባቸውም ።

ነገር ፡ ግን ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይቻላል ። ሰው ፡ ታምሞ ፡ ቢሆን ፡ ሳይታመምም ፡ ቢደክም ፡ ዞሮ ፡ ዞሮ ፡ በዚሁ ፡ የሚሞት ፡ ከሆነ ፡ አንድ ፡ ነው ። ባጭሩ ፡ የምርመራው ፡ ውጤት ፡ እንደዚህ ፡ ነው ። እኒህ ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ ደዌ ፡ የለባቸውም ።

ነገር ፡ ግን ፡ በቀድሞ ፡ ጉዳታቸው ፡ ምክንያት ፡ ደክመዋል ። እሳቸውም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ለመኖር ፡ የማይወዱ ፡ ስለሆነ ፡ የሚድኑበትን ፡ ነገር ፡ ኣይፈልጉም ። እንዲያውም ፡ ሞትን ፡ ይናፍቃሉ።

ስለዚህ ፡ ይድናሉ ፡ ተብሎ ፡ ተስፋ ፡ የለም ፡ ብለው ፡ አስታወቁ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልጆቹም ፡ በጣም ፡ አዝነው ፡ በጉዳትና ፡ በኃዘን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ በሽታቸው ፡ ስለተባለ ፡ በምግብም ፡ በሌላም ፡ ደስ ፡ በሚያሰኛቸው ፡ ነገር ፡ ለማስታመምና ፡ ለማዳን ፡ በጣም ፡ ደከሙ

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሽማግሌው ፡ በጣም ፡ ስለደከሙ ፡ አስተዳዳሪውን ፡ ጠርተው ፡ እባክህ ፡ ሳልሞት ፡ ልጆቼን ፡ ለማየትና ፡ ለመሰናበት ፡ እፈልጋለሁና ፡ ሦስቱንም ፡ ልጆቼን ፡ ጥራልኝ ፡ አሉት ።

አስተዳዳሪው ፡ ልጆችዎ ፡ እነማን ፡ ይባላሉ ፡ የስልካቸውስ ፡ ቁጥር ፡ ስንት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው

ሽማግሌውም ፡ ወይዘሮ ፡ አሰለፈች ፡ ወይዘሮ ፡ ውቢቱ ፡ ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ ይባላሉ ፡ አሉት ።

አስተዳዳሪውም ፡ እንደ ፡ ቅዠት ፡ መስሎት ፡ ተገርሞ ፡ እነሱማ ፡ ጌቶቻችን ፡ ናቸው ፡ አላቸው ።

ሽማግሌውም ፡ ግድ ፡ የለህም ፡ ጌቶቻችንም ፡ ልጆቻችንም ፡ ናቸው ። ጥራልኝ ፡ አሉት ።

አስተዳዳሪው ፡ ማን ፡ ጠራችሁ ፡ ብዬ ፡ ልንገር ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው።

ሽማግሌውም ፡ ያ ፡ የምትወዱት ፡ ሽማግሌ ፡ ብለህ ፡ ንገራቸው ፡ ያውቁታል ።

አስተዳዳሪውም ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ የዛሬ ፡ ሳምንት ፡ ለሠራተኛ ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ ሆስፒታል ፡ የሚጠሩት ሁሉ ፡ የምናስብላቸውና ፡ የምንወዳቸው ፡ ስለሆነ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ ለማንም ፡ ላንዳንድ ፡ ሰው ፡ አታድርጉ ፡ ለሁሉም ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ ሥሩላቸው። ብለው ፡ ጌቶቻችን ፡ ስላስተላለፉልን ፡ እርስዎን ፡ ብቻ ፡ የሚወድዋቸው ፡ ብለን ፡ ለማሳለፍ ፡ አንደፍርም ፡ አልዋቸው ።

ሽማግሌው ፡ እንግዲያው ፡ ልጆቼን ፡ በሆዴ ፡ እንዳረገዝኩ ፡ ሳልገላገል ፡ ልሞት ፡ ነውን ፡ እያሉ ፡ ስቅቅ ፡ ብለው ፡ ሲያለቅሱ ፡

ሦስቱም ፡ ልጆች ፡ እሳቸውን ፡ ለማሳየት ፡ አንድ ፡ ሐኪም ፡ ይዘው ፡ መጡ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሽማግሌው ፡ እያለቀሱ ፡ ሲያጥሩ ፡ ሦስቱም ፡ ልጆች ፡ ተጠግተው ፡ አባታችን ፡ ምን ፡ ሆኑ ፡ እያሉ ፡ ሲጠይቋቸው ፡ ቀና ፡ ብለው ፡ አይተው ፡ ልጆቼ ፡ መጣችሁ ፡ እንዳረገዝኋችሁ ፡ ልሞት ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ አዝኘ ፡ ነበር ። እግዚአብሔር ፡ እናንተን ፡ ካመጣልኝ ፡ ያረገዝሁትን ፡ ተገላግዬ ፡ እሞታለሁ ። ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ እኔን ፡ ታውቁኛላችሁን ።

ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ ከዚህ ፡ ከመጦሪያ ፡ ሆስፒታል ፡ ከገቡ ፡ ወዲህ ፡ ነው ፡ የምናውቀዎ ፡ አላቸው ።

ሽማግሌውም ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ምንም ፡ አታውቁኝም ፡ ሁሉም ፡ አናውቅዎትም ፡ አሉዋቸው ።

ሽማግሌው ፡ ወደ ፡ ሎንዶን ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ስትሔዱ ፡ የመከርኳችሁንና ፡ ተላቅሰን ፡ የተሰነባበትነው ፡ ትዝ ፡ አይላችሁምን ።

አሰለፈች ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ አባታችን ፡ ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምክር ፡ ከመከረን ፡ በኋላ ፡ ተላቅሰን ፡ መለያየታችንን ፡ አውቃለሁ ። እርስዎ ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ አብረው ፡ ነበሩን?

ሽማግሌው ፡ አብሬው ፡ ነበርኩ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ አባታችሁ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ የሚሉ ፡ ሰማችሁ ።

ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ጠፉ ፡ ማለትን ፡ ብቻ ፡ ከፈረንጅ ፡ አገር ፡ ሆነን ፡ ሰማን ።

ሽማግሌው ፡ ያጠፋፉን ፡ አኳኋን ፡ ምንም ፡ አታውቁትምን?

ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ አናቀውም ፡ እርሰዎ ፡ ያውቁት ፡ እንደሆነ ፡ ቢያጫውቱን ፡ ደስ ፡ ይለን ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ በጣም ፡ ስለደከመዎ ፡ ቢቀር ፡ ይሻላል ።

ሽማግሌው ፡ ግድ ፡ የለም ፡ ተቀመጡና ፡ ላጫውታችሁ ፡ ብለዋቸው ፡ እነሱም ፡ ሐኪሙም ፡ ከወንበር ፡ ላይ ፡ ተቀመጡ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሽማግሌው ፡ የተወደዳችሁ ፡ ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ አባታችሁ ፡ እናንተን ፡ ካሰናበተ ፡ በኋላ ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ቤቴን ፡ ዘግቶ ፡ ሌሊት ፡ ሌሊት ፡ በ፯ ፡ ሰዓት ፡ በሚያሳዝን ፡ የለቅሶ ፡ ዜማ ፡ ያለቅስ ፡ ነበር ።

ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ እባክዎ ፡ አባቴ ፡ ዜማውን ፡ ያውቁት ፡ እንደሆነ ፡ ይንገሩን ።

ሽማግሌው ፡ እሺ ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ ግጥሙን ፡ ልንገርህ ፡

ብፈልግ አጣኋት ፣ ካሽከሮች ፡ ቤት ፡
ፀሐይቱ ፡ መስፍን ፡ የውነት ፡ ወይዘሪት ፤
ምንስ ፡ ትዋረድ ፡ ብትወድቅ ፡ ከመሬት ፣
ባባትዋ ፡ መስፍን ፡ ናት ፡ በናትዋ እመቤት ፤
ዋኔን ፡ ዋኔን ፡ እኔ ፡ እፈር ፡ ልሁን ።

*****

በዚያ ፡ በዝናም ፡ ጐርፍ ፡ በሚያስፈራ ፡ ሴት ፡
ብቻዋን ፡ ስትሮጥ ፡ ልጅዋን ፡ ማየት ፤
ስትወድቅ ፡ ስትነሣ ፡ የስማዩ ፡ ቁጣ ፡ እንደ፡ ቦምብ ፡ ሲበርቅ ፡ ደረሰች ፡ ካቃቂ ፡ በአሳር ፡ በጭንቅ ፤
ዋኔን ፡ ዋኔን ፡ እኔ ፡ አፈር ፡ ልሁን ።

*****

ቆረጠች ፡ መውደቅ ፡ ከባሕሩ ፡ ላይ ፡
ተስፋዬን ፡ ከመሬት ፡ ወድቆ ፡ እንዳታይ ፤
ወዳጄ ፡ ፀሐይነሽ ፡ ሳይሽ ፡ መጣሁኝ ፡
ታመሻል ፡ የሚሉ ፡ ስለሰማሁኝ ፤
ዋኔን ፡ ዋኔን # እኔ ፡ አፈር ፡ ልሁን ፡ ፡

*****

አንቺ ፡ ግን ፡ እስርግሽ ፣ መጣሽ ፡ አጊጠሽ ፡
ዓይንሽን ፡ አየሁት ፡ ሞትን ፡ ተኩለሽ

ዘወትር ፡ የማይሻር ፡ የልብ ፡ ነቀርሳ፤
በኔ ፡ የደረሰው ፡ የነፍስ ፡ ወቀሳ
ደህና ፡ ሰንብት ፡ አልሺኝ ፡ ልጆቼን ፡ ስጥተሺ
እኔ ፡ እንዳንቺ ፡ ሆኜ ፡ የማልሞት ፡ መስሎሽ ፡
ዋኔን ፡ ዋኔን ፡ እኔ ፡ አፈር ፡ ልሁን ፡ ፡
*****

ወይዘሮ ፡ አሰለፈች ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ እንደምን ፡ ሆነ ፡

ሽማግሌው ፡ ከዚያ በኋላማ ፡ ከመኝታው ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ አንዲት ፡ ወረቀት ፡ ጽፎ ፡ ጥሎ ፡ በሩን ፡ ዘግቶ ፡ ጠፋ ።

ወይዘሮ ፡ ውቢት ፡ ምንድነው ፡ የጻፈው ፡ ቃል ፡ አለችው ።

ሽማግሌው ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ዘመዱ ።
መች ፡ ይስኖል ፡ ወዳጅ ፡ ርቀው ፡ ሲሔዱ ።

የሚል ፡ ቃል ፡ ነው ።

ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ ይህነን ፡ ጽፎ ፡ ወዴት ፡ ሔደ?

ሽማግሌው ፡ ይህንኑ ፡ ግጥም ፡ እያንጐራጐረ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ማይደርስበት ፡ በረሃ ፡ ሔዶ ፡ ተቀመጠ

ወይዘሮ ፡ አሰለፈች ፡ እባክዎ ፡ ከዚያ ፡ ከበረሃ ፡ የሚባሉ ፡ አውሬዎች ፡ የሉምን ።

ሽማግሌው ፡ ብዙ ፡ ተናጣቂ ፡ አውሬዎች ፡ አሉ ። ለምሳሌ ፡ አንበሳ ፡ ነብር ፡ ጅብ ፡ ከነሱም ፡ ይልቅ ፡ በጣም ፡ የከፉ ፡ ዬዬ ፡ የሚባሉ ፡ ብዙ ፡ ሆነው ፡ መጥተው ፡ የሚበጫጨቁ ፡ አሉ ።

ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ እባክዎ ፡ አባቴ ፡ እሱን ፡ እንደምን ፡ ሳይበሉት ፡ ቀሩ ።

ሽማግሌው ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ሰው ፡ በውነት ፡ ከቆረጠና ፡ እምነቱን ፡ እንደ ፡ ብረት ፡ ካጠነከረ ፡ ተናጣቂ ፡ አውሬዎችም ፡ ስንኳ ፡ ተገዥዎቹ ፡ ይሆናሉ ።

ሰሎሞን ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ደቦል ፡ አንበሳ ፡ ብቻውን ፡ ቢሔድ ፡ ማንንም ፡ አይፈራም ፡ ይላል

መድኃኒታችንም ፡ የሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ የሚያህል ፡ ሃይማኖት ፡ ቢኖራችሁ ፡ ይህንን ፡ ተራራ ፡ ተነስተህ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ሒድ ፡ ለማለት ፡ ትችላላችሁ ፡ ብሎዋል ።

ስለዚህ ፡ ያባታችሁ ፡ ሃይማኖት ፡ የጠነከረ ፡ ስለሆነ ፡ አውሬዎቹን ፡ ሁሉ ፡ በመንፈሱ ፡ ገዝቶዋቸው ፡ ነበር ።

በዚያ ፡ በበረሃ ፡ ውስጥ ፡ አባታችሁን ፡ ተናጣቂና ፡ ግሩማህን ፡ የሆኑ ፡ አውሬዎች ፡ ከበውት ፡ ሲታይ ፡ አባታችን ፡ አዳም ፡ የፍጡራን ፡ ሁሉ ፡ ጌታ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ በገነት ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ አኳኋን ፡ ይታይ ፡ ነበር ።

ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ እንደምን ፡ ሆነ

ሽማግሌው ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ልጆቹ ፡ ከተማሪ ፡ ቤት ፡ ትምህርታቸውን ፡ ጨርሰው ፡ መምጣታቸውን ፡ በሕልሙ ፡ ስላየ ፡ እነሱን ፡ ለማየትና ፡ ያወረሳቸውን ፡ ገንዘብ ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ ማዋላቸውን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ መጣ ።

ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ አባታችን ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ መጥቶ ፡ ሳያየን ፡ ለምን ፡ ሔደ?

ሽማግሌው ፡ ሳያያችሁስ ፡ አልሔደም ፡ ከመልካም ፡ ሥራችሁ ፡ ላይ ፡ አይቶዋችኋል ። እያለ ፡ ያለቅስ ፡ ጀመር ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ ብድግ ፡ ብለ ፡ ካጠገቡ ፡ ቀርበው ፡ መቼ ፡ ነው ፡ ያየን ፡ እያሉ ፡ ሲጠይቁት ፡ በሚያሳዝን ፡ በድካም ፡ ቃል ፡ አሁንም ፡ የማያችሁ ፡ እኔ ፡ አባታችሁ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ ነኝ ። እንግዲህ ፡ አደራችሁን ፡ ከንጽሕና ፡ ሚስቴ ፡ ጋር ፡ ካቃቂ ፡ ወስዳችሁ ፡ ከፀሐይ ፡ መስፍን ፡ ጋር ፡ ቅበሩኝ ፡ ብሎ ፡ ወዳጅ ፡ ሲመጣ ፡ ፍግግ ፡ ብሎ ፡ እንደሚቀበል ፡ ሰው ፡ ዓይኑን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ሰክቶ ፡ የኔ ፡ ጌታ ፡ እጅህን ፡ ዘርግተህ ፡ ልትቀበለኝ ፡ መጣህ ፡ ብሎ ፡ ከትራሱ ፡ በታች ፡ አንገቱን ፡ አዘንብሎ ፡ አረፈ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ልጆቹ ፡ ቆመው ፡ ይመለከቱ ፡ ነበርና ፡ ጮኸው ፡ ከላዩ ፡ ላይ ፡ ወድቀው ፡ ሲስሙት ፡ ሦስቱም ፡ ልጆች ፡ በኃዘንና ፡ በድንጋጤ ልባቸው ፡ ቆሞ ፡ ካልጋው ፡ሥር ፡ ወደቁ ።

ሐኪሙም ፡ በጣም ፡ ደንግጦ ፡ ላባታቸው ፡ ያመጣውን ፡ የልብ ፡ ብርታት ፡ መድኃኒት ፡ ወጋቸውና ፡ ታቅፈው ፡ ወስደው ፡ ከዚያው ፡ ከሆስፒታል ፡ ሦስቱንም ፡ ልጆቹን ፡ አስተኝዋቸውና ፡ ሐኪሙ ፡ ልጅ ፡ ዓለሙን ፡ ጨርሶ ፡ ኣርፎ ፡ እንደሆን ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ምርመራ ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ ቶሎ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ወስደው ፡ አጥበው ፡ ገንዘው ፡ ለመኳንንቱና ፡ ለመሳፍንቱ ፡ ለሚኒስትሮቹ ፡ በስልክ ፡ ይህንን ፡ የሚገርም ፡ የተአምር ፡ ሥራ ፡ አሳለፉ ።

ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ስንኳን ፡ መኳንንቱና ፡ መሳፍንቱ ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ያሉ ፡ ትንሹም ፡ ትልቁም ፡ ሕዝብ ፡ የልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታንና ፡ የፀሐይ ፡ መስፍንን ፡ የተአምራት ፡ ሥራ ፡ የማያውቅ ፡ ሰው ፡ ስለሌለ ፡ የከተማው ፡ ሰው ፡ በሙሉ ፡ ከልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ቤት ፡ ድረስ ፡ መጥቶ ፡ ዓፅሙ ፡ ሙሉ ፡ ፍታት ፡ ከተደረገለት ፡ በኋላ ፡ አቃቂ ፡ ከፀሐይ ፡ መስፍን ፡ መቃብር ፡ ወስደው ፡ ቀበሩት ።

ሴቶቹ ፡ ልጆች ፡ በጣም ፡ ልባቸው ፡ በኃዘን ፡ ስለተመታ ፡ ለመነሣትና ፡ አባታቸውን ፡ ለመቅበር ፡ ባለመቻላቸው ፡ ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ ብቻ ፡ ጥቂት ፡ ስለተሻለው ፡ አባቱን ፡ አስቀብሮ ፡ ወደቤቱ ፡ ተመለሰ።

አንባቢ ፡ ሆይ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ወዳጁ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ለልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ የመከራ ፡ ጓደኛው ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ በመከራው ፡ ሁሉ ፡ ሳይለየው ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የነፍስና ፡ ሥጋ ፡ ታሪካዊ ፡ ስም ፡ አሰጠው ።

ከመቃብር ፡ ድረስ ፡ ስንኳን ፡ የማይሸኘን ፡ ወዳጃችን ፡ ገንዘብም ፡ በብልሐት ፡ ስለተያዘ ፡ በቁም ፡ ነገር ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ስላገኘው ፡ ልጅ ፡ ዓለሙ ፡ ደስታ ፡ መጠን ፡ የሌለው ፡ ደስታ ፡ ተሰማው ።

ገንዘባችሁ ፡ ባልሆነው ፡ ገንዘብ ፡ ወዳጅ ፡ ግዙበት ፡ ያለውን ፡ የመድኃኒታችንን ፡ ቃል ፡ ልጆቹ ፡ ፈጽመው ፡ ስላገኛቸው ፡ መርቆ ፡ የሰላም ፡ እንቅልፍ ፡ አንቀላፉ ።

ገንዘብ ፡ የልብ ፡ ሥር ፡ ስለሆነ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ዘወትር ፡ ገንዘቡ ፡ ካለበት ፡ ልቡም ፡ ከዚያው ፡ ስለሚሆን ፡ ገንዘብን ፡ አስቀድሞ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ መላክ ፡ ዋና ፡ የልብ ፡ ዕረፍትን ፡ ይሰጣል ።

በምድር ፡ የተከማቸ ገንዘብ ፡ ግን ፡ በመቃብራችን ፡ ውስጥ ፡ እሳት ፡ ሆኖ ፡ ሥጋችንን ፡ እንደ ፡ ሚበላው ፡ ያዕቆብ ፡ ሐዋርያው ፡ ጽፎታል ።



## ስለደራሲው በጥቂቱ

ራስ ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው በሰሜን ሸዋ በተጉለት አውራጃ አዲስጌ በምትባል ቦታ በ በ1983 ዓ.ም. ተወለዱ፡፡ በዳግማዊ ምኒልክ፣ በንግሥት ዘውዲቱ እና በዓፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥታት በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሀገራቸውን አገልግለዋል።

በሕይወት ዘመናቸው ከ20 በላይ መጻሕፍት በመድረስ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ዕድገት የጎላ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ ከሥነ ጽሑፍ ሥራዎቻቸው ውስጥ የታተመው "አርሙኝ" የተባለው መጽሐፋቸው በብዙዎች ዘንድ የታወቀ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ የሕይወት ታሪካቸውን ባጭሩ፣ እንዲሁም በተለያዩ ጊዜያት የጻፏሕውን ድርሰቶችን ስለማይጮው ጦርነትና የዓለም ፖለቲካ በማካተት የጻፉት ነው፡፡ "የድሆች ከተማ" በ1933፣ "ሐሳብና ሰው" በ1933፣ "ሣልሳዊ ዳዊት" በ1933 "የፍቅር ጮራ" በ1939፣ ከጻፏቸው መጽሐፍት መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

**ምንጭ**: የኢትዮድያ ደራሲያን ማህበር ለሚሊኒየም ያሳተመው አጀንዳ።

<u>የደራሲው ሥራዎች</u>

1. ያይኔ አበባ(ልብወለድ)
2. አልሞትኹም ብዬ አልዋሽም(ተውኔት)
3. ተዎድሮስ ጣይቱ ብጡል(ልብወለድ)
4. ዦሮ ጠቢ(ልብወለድ)
5. የድኾች ከተማ(ልብወለድ)
6. ፀሓይ መስፍን(ልብወለድ)
7. መልካም ቤተሰቦች(ታሪክ)
8. ሣልሳዊ ዳዊት(ተውኔት)
9. አርሙኝ(ፍልስፍና)
10. የቃየል ድንጋይ(ተውኔት)
11. ዓለም ወረተኛ(ተውኔት)
12. የደም ድምፅ(ተውኔት)
13. አሳብና ሰው(ተውኔት)
14. የማይጨው ጦርነት ባጭሩ የዓለም ታሪክ(ታሪክ)
15. ከቡቃያ እስከ መከር(ልብወለድ)

16. የሕልም ሩጫ (ታሪክ)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY